# መጽሐፈ ሳሙኤል ካልእ

ይህ መጽሐፍ የዳዊትን 40 ዓመት ንግሥና የሚተርክ መጽሐፍ ነው:: 7 ዓመት በኬብሮን (በይሁዳ ላይ) ነገሠ 33 ዓመት ደግሞ በእስራኤል ሁሉ ላይ ነገሠ:: ይህ መጽሐፍ በሳሙኤል ስም ቢሰየምም ሳሙኤል ከሞተ በኋላ ያለውን ታሪክ የሚተርክ ስለሆነ በሳሙኤል አለመጻፉ ግልጽ ነው:: ይህንን መጽሐፍ ጻፉ ተብሎ የሚታመነው ነቢዩ ናታንና ጋድ ናቸው:: 1ዜና መዋዕል 20፥29-30

## ይህ መጽሐፍ ለሁለት ይከፈላል፡ -

1. የዳዊት መንገሥና ድል- (ከምዕ. 1-10)

   ሀ. በይሁዳ ላይ መንገሡ (ከምዕ 1-4)

   ለ. በእስራኤል ሁሉ ላይ መንገሡ ከምዕ. 5-10)

   ይህ ክፍል ዳዊት በእስራኤል ላይ የነበረውን የክብርና የድል ዘመን ያሳያል

2. የዳዊት ኃጢአትና መውደቅ፡ - (ከምዕ. 11-24)

   ሀ. የዳዊት በዝሙት ኃጢአት መውደቅ (ምዕ. 11-12)

   ለ. ዳዊት በቤተሰቡ (በልጆቹ) ያጋጠመው ችግሮች (ከምዕ. 13-18)

   ሐ. ዳዊት በአገሩ በእስራኤል ያጋጠመው ችግሮች (ከምዕ. 19-24)

## የዚህ መጽሐፍ ዋና ማዕከላዊ መልእክት፡ -

ለእግዚአብሔር መታዘዝ በረከትንና ድልን እንደሚያስገኝ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ላይ ማመጽ (ኃጢአት) ደግሞ ውድቀትንና ችግርን እንደሚያስከትል:: በአጭሩ፤ የዳዊት ኀጢአት እንዴት በረከቱንና ሕይወቱን መራራና በችግር የተሞላ እንዳደረገበት እናያለን::

ክፍል 1- <u>የዳዊት መንገሥና ድል</u> (<u>ምዕ. 1-10</u>)

ምዕ. 1 በዚህ ምዕራፍ የምናየው ዳዊት ስለ ሳዖልና ዮናታን መሞት መርዶ ሲደርሰውና፣ ለቅሶና የኃዘን እንጉርጉሮ ሲያደርግ ነው::

ከዚህ ምዕራፍ ስለዳዊት የበለጠ መረዳት እንችላለን:: ምንም እንኳን ሳዖል ለብዙ ዓመታት እንደ ቆቅ ሲያሳድደው ቢኖር፣ እግዚአብሔር ሳዖልን በጠላቶቹ ፊት ጥሎት ከወደቀ በኋላ እንኳን እግዚአብሔር በጠላቴ ላይ ተበቀለልኝ ብሎ ደስ አልተሰኘም:: እንደውም ልክ እንደ ወዳጁ ቅኔ ሲቀኝለት እናነባለን:: የሳዖልን ክፉ ሳይሆን መልካሙን ብቻ አስታወሰ:: በቁ. 20 ላይ ዳዊት ለሳዖልና ዮናታን በተቀኘው ቅኔ ውስጥ እንዲህ ይላል፤

«የፍልስጥኤማውያን ቆነጃጅት ደስ እንዳይላቸው የቆላፋንም ቆነጃጅት እልል እንዳይሉ በጌት ውስጥ አታውሩ
በአስቀሎናም አደባባይ የምሥራች አትበሉ፡፡»

በዚህ ጥቅስ ውስጥ ትልቅ መልእክት አለ፡፡ በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል ወይም በሕይወታችን መሸነፍ በሚመጣበት ጊዜ ማውራት እንደሌለብን ያስተምረናል፡፡ በተለይ የጠላት ጆሮ በሚሰማበትና ጠላት ደስ በሚሰኝበት ሁኔታ ማውራት የለብንም፡፡ ብናወራ በጸሎትና በፍቅር ለሚደግፉን ሰዎች ብቻ መሆን አለበት፡፡ እንደዚህ ዓይነት ሰው ካጣን በእኛና በእግዚአብሔር መካከል ብቻ ነገሩ እንዲቀር ማድረግ፡፡

ዳዊት በቅኔው ውስጥ የጠቀሳቸው ሁለት ከተማዎች የፍልስጥኤማውያን ከተማዎች ናቸው፡፡ በጠላት ሠፈር መሸነፋችሁን አታውሩ ማለት ነው፡፡

ምዕ. 2 ይህ ምዕራፍ ዳዊት እግዚአብሔርን ከጠየቀ በኋላ የይሁዳ ከተማ ወደሆነችው ወደ ኬብሮን እንደሄደና በዚያ የይሁዳ ሰዎች በይሁዳ ቤት ላይ ይነግሥ ዘንድ እንደ ቀቡት፤ እንዲሁም የሳዖል የጦር አዛዥ የነበረው አበኔር የሳዖልን ልጅ ኢያቡስቴን በእሥራኤል ላይ ንጉሥ እንዳደረገው እናነባለን፡፡ ከቁ. 12-32 የምናየው በሳዖል ሠራዊቶችና በዳዊት ሠራዊቶች መካከል ጦርነት እንደተደረገ ነው፡፡

ከቁ. 1-4 የምናየው፡ -ምንም እንኳን ጊዜው የእስራኤል ንጉሥ ሳዖልና ልጁ የሞቱበትና በእስራኤል ላይ ንጉሥ የሌለበት ጊዜ ቢሆንም፤ ዳዊት አሁን ባዶ ዙፋን አገኘሁ ሂጄ ልንገሥ ሳይል «ከይሁዳ ከተሞች ወደ አንዲቱ ልውጣን? ብሎ እግዚአብሔርን ጠየቀ፡፡ እግዚአብሔርም ውጣ አለው፡፡ ዳዊትም፡ - ወዴት ልውጣ አለ፡ እርሱም፡ ወደ ኬብሮን ውጣ አለው» (ቁ. 1) ወደ ኬብሮን ከወጣ በኋላ ራሱን አላነገሠም፤ ነገር ግን «የይሁዳ ሰዎች መጥተው በይሁዳ ቤት ፡፡ይነግሥ ዘንድ ዳዊትን በዚያ ቀቡት፡፡» (ቁ. 4) በእግዚአብሔር ቤት ስንመላለስ በምንም ነገር ላይ ራሳችንን እንዳንሾም መጠንቀቅ አለብን እግዚአብሔርና ሕዝቡ እስኪቀቡን መጠበቅ አለብን፡፡

በ1ሳሙ. 16÷13 እግዚአብሔር በነቢዩ ሳሙኤል በኩል ቀባው
በዚህ ምዕራፍ ቁ. 4 ላይ የይሁዳ ሰዎች ቀቡት
በምዕ. 5÷3 ላይ፡ - በእስራኤል ሁሉ ላይ ንጉሥ ይሆን ዘንድ የእስራኤል ሽማግሌዎች ቀቡት

ከቁ. 12-32 በሳዖል የተጀመረ መዘዝ በዳዊትና በሳዖል ጭፍሮች መካከል የርስበርስ ጦርነት ሲያስነሳና ብዙዎች ሲሞቱ እናያለን፡፡ ሳዖል ከጅምሩ በዳዊት ላይ በምቀኝነት ባይነሳ ኖሮ ይህ የእርስ በርስ ጦርነት ባልኖረ ነበር፡፡ በዚህ ክፍል የምናየው፡ - በመሪዎች መካከል ጦርነትና ቀውስ ሲኖር የእግዚአብሔር ሕዝብ እርስ በርሱ እንዲቆራቆስ ይደረጋል፡፡

«አበኔርም ኢዮአብን፡ - ጎልማሶች ይነሡ በፊታችንም ይቆራቆሱ አለው ... ሁሉም እያንዳንዱ የወደረኛውን ራስ ያዘ፣ ሰይፉንም በወደረኛው ጎን ሻጠ <u>ተያይዘውም ወደቁ</u>፡፡»

ብዙዎች ከወደቁ በኋላ «አበኔር ወደ ኢዮአብ ጮኽ ሰይፍ በውኑ እስከ ዘላለም ያጠፋልን? ፍጻሜውስ መራራ እንደሆነ አታውቅምን? ሕዝቡ ወንድሞቻቸውን ከማሳደድ ይመለሱ ዘንድ ሕዝቡን የማትነግር እስከ መቼ ነው? አለው፡፡» ከድሮውም ጠቡን የጫረው እርሱ ራሱ ነበር፡፡ አሁን ግን የእርሱ ወገን የበለጠ እንደተጠቃ ሲያይ ሕዝቡ ወንድሞቻቸውን ለምን ያሳድዳሉ? ብሎ ይጠይቃል፡፡ ይህንን ማለት የነበረበት ከጅምሩ ነበር፡፡

«ኢዮአብም ቀንደ መለከት ነፋ ሕዝቡም ሁሉ ቆመ፣ ከዚያም በኋላ እስራኤል አላሳደደም። ሰልፍም አላደረገም።» ከዚህ ክፍል የምናየው፤ የእግዚአብሔር ሕዝብ እርስ በርሱ እንዲዋጋም ሆነ ከመዋጋት እንዲገታ የማድረግ ሥልጣንና ኃላፊነት የነበራቸው የጦር መሪዎቹ ነበሩ። በእግዚአብሔርም ቤት ውስጥ ሕዝቡ እርስ በርሱ እንዲባላም ሆነ በሰላምና በዕርቅ እንዲኖር የሚያደርጉ መሪዎች ናቸው። በዚህ ዘመን በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ የጠፉት የዕርቅን፣ የሰላምንና የፍቅርን መለከት የሚነፉ መሪዎች ናቸው። የጦርነትን የመከፋፈልንና የጥላቻን መለከት የሚነፉ ግን ብዙዎች አሉ።

## ምዕራፍ ሦስት

ይህ ምዕራፍ፣ የሳኦል የጭፍራ አለቃ በነበረው በአበኔርና በእስራኤል ላይ ነግሦ በነበረው በኢያቡስቴ መካከል አለመግባባት ተፈጥሮ እንደተጣሉና በዚህ ጥል ምክንያት አበኔር እስራኤልን ሁሉ ለዳዊት ለመመለስ በኢያቡስቴ ላይ ሲዝት ያሳያል።

መቼም እግዚአብሔር በወጀብና በዐውሎ ነፋስ እንኳን መንገድ ስላለው የእነዚህን ሁለት ሰዎች ጥል ተጠቅሞ ዳዊት በእስራኤል ላይ የሚነግሥበትን መንገድ ሲያዘጋጅለት እናያለን። እግዚአብሔር አንድን የተስፋ ቃል ከሰጠን ያለ እኛ እርዳታ ራሱ በራሱ ጊዜ የሚፈጽምበት መንገድ አለው።

በቁ. 1 ላይ ፡ - «በሳዖልና በዳዊት ቤት መካከል ብዙ ዘመን ጦርነት ሆነ፤ የዳዊት ቤት እየበረታ፣ የሳዖል ቤት ግን እየደከመ የሚሄድ ሆነ» ይላል።

ይህ ጥቅስ በሕይወታችን በሥጋና በመንፈስ መካከል ያለውን የማያቋርጥ ጦርነት ያመለክታል።

ገላ 5፥17 «ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና እነዚህም እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ።» በገላ 4፥21-31 ስለ አጋርና ሣራ እንዲሁም ከእነርሱ ስለተወለዱት ስለ እስማኤልና ይስሐቅ ሲናገር «ነገር ግን እንደ ሥጋ የተወለደው (እስማኤል) እንደ መንፈስ የተወለደውን በዚያን ጊዜ እንዳሳደደው ዛሬም እንዲሁ ነው።» (ቁ. 29) ይላል።

በዚህም ምዕራፍ፤ እንደ ሥጋ ፈቃድ ይነዳ የነበረው ሳዖል እንደ መንፈስ ፈቃድ ይመራ የነበረውን ዳዊትን ለብዙ ዘመናት እንዳሳደደው፤ ነገር ግን፣ ዳዊት እየበረታ የሳዖል ቤት ግን እየደከመ እንደሄደ ያሳየናል። በእኛም ሕይወት የሚካሄደው የሥጋና የመንፈስ ውጊያ እኛ ለእግዚአብሔር ታዛዥና ታማኝ በሆንን መጠን መንፈስ እየበረታ ሥጋ ደግሞ እየደከመ እንደሚሄድ ያመለክታል።

በተጨማሪም፤ በዚህ ምዕራፍ የዳዊት የጭፍራ አለቆች የነበሩት ወንድማማቾች፣ ኢዮአብና አቢሳ በአቤኔር ተገድሎ ለነበረው ወንድማቸው ተበቅለው አበኔርን እንደገደሉት እናያለን። ዳዊት ግን ከአበኔር ደም ንፁህ እንደሆነ ለእስራኤል ሁሉ ያሳውቃል።

## <u>ምዕራፍ አራት</u>

በዚህ ምዕራፍ የምናየው የእስራኤል ንጉሥ የነበረው የሳዖል ልጅ ኢያቡስቴ የጭፍራው አለቆች በነበሩት በዓናና ሬካብ በሚባሉ ሁለት ሰዎች ሲገደልና ዳዊት በእነርሱ ላይ በቀል ሲፈጽምባቸው ነው።

በቁ. 4. ላይ አንዲት የዮናታን ልጅ ሞግዚት የነበረች ሴት ፈጥና በምትሸሽበት ጊዜ አዝላ የነበረችው ልጅ ወድቆ ሽባ እንደሆነ እናነባለን። ይህ ሁኔታ በአጋጣሚ የሆነ አደጋ

ቢሆንም በመንፈሳዊ አመለካከት በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ እግዚአብሐር በመንፈስ ህፃናት የሆኑትን እንዲጠብቁ ያስቀመጣቸው መንፈሳዊ ሞግዚቶች በጥንቃቄ የእግዚአብሔርን ግልገሎች ካልጠበቁ ከእጃቸው ወድቀው ዕድሜ ልካቸውን ሽባ መሆን ይችላሉ። በቁ. 8 ላይ በዓናና ሬካብ ጌታቸውን በግፍ ከገደሉ በኋላ ወደ ዳዊት የኢያቡስቴን ራስ ይዘው መጥተው «... እግዚአብሔርም ዛሬ ከሳዖልና ከዘሩ ለጌታችን ለንጉሡ ተበቀለለት አሉት።» የሚል ቃል እናነባለን። የእነዚህ አመጸኞች ቃል በጣም የሚገርመው ንጉሣቸውን ኢያቡስቴን ለመጠበቅ የተሾሙ የጭፍራ አለቆች ሆነው ሳሉ በዓመፅ በተኛበት ገድለውና ራሱን ቆርጠው ለዳዊት «እግዚአብሔር ተበቀለልህ» ይሉታል። ብዙ ጊዜ ሰዎች የራሳቸውን የአመፅ ሥራ እግዚአብሔር እንዳደረገው የጽድቅ ሥራ አድርገው ይናገራሉ። ዳዊት ግን በከንቱ ውዳሴና ጽድቅ በሚመስል አመጽ ስለማይታለልና እንደ እግዚአብሔር ልብ የሆነ ልብ ስለነበረው ለኢያቡስቴ ደም ተበቅሎ ሲያስገድላቸው እናያለን። እግዚአብሔር ግን በወጀብና በዓውሎ ነፋስም መንገድ ስላለው በዚህ ሁሉ ለዳዊት መንገድን ሲጠርግለትና በእሥራኤል ሁሉ ላይ ይነግሥ ዘንድ ሁኔታዎችን ሲያመቻችለት እናያለን።

በቁ. 9 ላይ ዳዊት እግዚአብሔርን ለመጥራትና ለመማል የተጠቀመበትን ሐረግ ስንመለከት ዳዊት ምን ያህል ከእግዚአብሔር ጋር የተጣበቀ እንደነበረ እንረዳለን። «<u>ነፍሴን ከመከራ ሁሉ ያዳነ</u> ሕያው እግዚአብሔርን» ከዚህ አባባል ትልቅ ትምህርትን እናገኛለን። ዳዊት ከመከራ ሁሉ <u>የጠበቀኝ</u> አላለም፣ ነገር ግን ከመከራ ሁሉ ያዳነኝ ነው ያለው። ያዳነኝ ሲል በመከራ ውስጥ ማለፉን ያመለክታል። እግዚአብሔር መከራ ውስጥ እንዳንገባ መጠበቅ ሳይሆን በሚያገኘን መከራ ሁሉ በድል እንድናልፍ ከምንገባበት መከራ ሁሉ እንደሚያድነን ያሳያል። ስለዚህ ነው በመዝ 34÷19
«የጻድቃን መከራቸው ብዙ ነው
እግዚአብሔርም <u>ከሁሉ</u> ያድናቸዋል።» ያለው።

## ምዕራፍ አምስት

በዚህ ምዕራፍ የእስራኤል ሽማግሌዎች ዳዊትን በእስራኤል ላይ ንጉሥ እንዲሆን ሲቀቡት፣ ለብዙ ዘመናት በኢየሩሳሌም ይኖሩ የነበሩትን ኢያቡሳውያንን ድል ሲያደርግ፣ እንዲሁም የጢሮስ ንጉሥ ኪራም ለዳዊት ቤት ሲያሠራለት እና በመጨረሻም ዳዊት ፍልስጥኤማውያንን ሁለት ጊዜ ድል ሲያደርግ እናነባለን።

ከቁ. 1-5 የእስራኤል ሽማግሌዎች ዳዊትን በእስራኤል ሁሉ ላይ ንጉሥ ይሆን ዘንድ ቀቡት። ሲያነግሡት እናነባለን። ከዚህ በፊት እንደጠቀስነው እግዚአብሔር ዳዊትን በሳሙኤል አማካይነት በ1ሳሙ. 16 ላይ ንጉሥ እንዲሆን ከቀባው በኋላ በብዙ ውጣ ውረድና መከራ አሳልፎ በመጀመሪያ በይሁዳ ላይ ብቻ ለሰባት ዓመት ተኩል ከዚያም በእስራኤል ሁሉ ላይ ለሠላሳ ሦስት ዓመታት ሲያነግሡት እናያለን። ዳዊት መቼም ቢሆን እግዚአብሔር ንጉሥ እንድሆን ቀብቶኛልና በእናንተ ላይ ልንገሥ ብሎ ሊነግሥ ሲሞክር አናይም፣ ነገር ግን ሰዎቹ ራሳቸው እየመጡ በእነርሱ ላይ እንዲነግሥ ሲቀቡትና ሲለምኑት ነው የምናየው።

ከቁ. 6-10 ዳዊት ኢያቡሳውያንን ተዋግቶ ሲያወጣና እነርሱ ይዘዋት የነበረችውን ከተማ «የዳዊት ከተማ» ብሎ ሲሰይማት እናያለን። እነዚህ ኢያቡሳውያን ከኢያሱ ዘመን ጀምሮ ከእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል የያዝነውን ሥፍራ አንለቅም ብለው ከተማቸውን መሽገው ይኖሩ የነበሩ እስከዚህ ጊዜ ድረስ ማንም ሊያወጣቸው ያልደፈረ ሕዝብ ናቸው።

«በኢየሩሳሌም የተቀመጡትን ኢያቡሳዊያንን ግን የይሁዳ ልጆች ሊያሳድዷቸው <u>አልተቻላቸውም</u> ኢያቡሳውያንም እስከ ዛሬ ድረስ በይሁዳ ልጆች መካከል በኢየሩሳሌም ውስጥ ተቀምጠዋል።» መጽሐፈ ኢያሱ 15÷63።

በ2ሳሙ. 5÷6 - «ንጉሡና ሰዎቹም በአገሩ ውስጥ ከተቀመጡት ከኢያቡሳውያን ጋር ለመዋጋት ወደ ኢየሩሳሌም ሄዱ፡፡» የሚል ቃል እናነባለን፡፡ ከዚህ ጥቅስ የምናየው፤ እግዚአብሔር በሰጠን ርስትና አገር ውስጥ ሥፍራዬን አልለቅም ብሎ፣ ማን ደፍሮ ያስወጣኛል? በማለት የሚገዳደር ጠላት ሊኖር እንደሚችል ነው፡፡ በእግዚአብሔር በኩል ኢየሩሳሌም ለብንያም ወገን ተሰጥታ የነበረች ከተማ ነች (ኢያሱ 18÷27)፡፡ ነገር ግን ማንም ደፍሮ ይህንን ርስት ለመጨበጥ የተቻለው ሰው አልነበረም፡፡ ዳዊት እስኪመጣ ድረስ፡፡ በእኛም በእያንዳንዳችን ሕይወት እግዚአብሔር እንድንወርሰው ሰጥቶን ሳለ ተዋግተን ለመውረስ እምነቱም ሆነ ትጋቱ ስለሚጎድለን በጠላት ቁጥጥር ስር እንዳለ የሚኖር ስንት ርስት ይኖር ይሆን? እግዚአብሔር የዳዊትን መንፈስ ይስጠን፡፡

ከቁ. 11-12 የአሕዛብ ንጉሥ የነበረ የጢሮስ ንጉሥ ኪራም ለዳዊት ቤት ሲሠራለት እናያለን፡፡ «ዳዊትም እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ ንጉሥ አድርጎ እንዳጸናው ስለ ሕዝቡ ስለ እስራኤልም መንግሥቱን ከፍ እንዳደረገ አወቀ» (ቁ. 12)፡፡ በቁ. 3 ላይ የእስራኤል ሽማግሌዎች በእስራኤል ላይ ንጉሥ እንዲሆን ቢቀቡትም፣ «እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ ንጉሥ አድርጎ እንዳጸናው አወቀ፡፡» ነው የሚለው፡፡ ሰዎች ምንም ከፍ ቢያደርጉንና ቢቀባቡን፣ ያ ሙገሳና ቅባት ከእግዚአብሔር መሆን አለመሆኑን ማረጋገጥ አለብን፡፡ ዳዊት፣ እግዚአብሔር መንግሥቱን ያጸናለት ስለ እርሱ ማንነት ሳይሆን «ስለ ሕዝቡ ስለ እስራኤል» እንደሆነ የተረዳ ሰው ነበር፡፡ እግዚአብሔር ጸጋውንና ቅባቱን ሲያበዛልን እኛ ከሌሎች ተሽለን ወይም ከሌሎች የበለጠ ጻድቃን ሆነን ሳይሆን ስለ ሕዝቡ ሲል እንደሆነ መረዳት አለብን፡፡ እግዚአብሔር ሕዝቡን ሊባርክ፣ ሊፈውስ፣ ሊቀድስና ሊጎበኝ ሲፈልግ ማናችንንም ሊጠቀም ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ ትሕትናና «እኛ የማንጠቀም ባሪያዎች ነን» የሚል መንፈስ ሊኖረን ይገባል እንጂ በእግዚአብሔር ጸጋ ልንኩራራ አይገባም፡፡ አለበለዚያ ውድቀታችን የፈጠነ ይሆናል፡፡

ከቁ. 17-25 ዳዊት ሁለት ጊዜ ፍልስጥኤማውያንን ሲመታ እናያለን፡፡ «ፍልስጥኤማውያንም ዳዊት በእስራኤል ላይ ንጉሥ ሆኖ እንደ ተቀባ ሰሙ  ዳዊትን ሊፈልጉ ወጡ» (ቁ. 17)፡፡ ጠላት ሁልጊዜ የሚፈልገው ቅባት ያለባቸውን ሰዎች ነው፡፡ የእግዚአብሔር ቅባት በሌለባቸው ሰዎች ላይ ጊዜውንም ሆነ ኃይሉን አያባክንም፡፡ ዳዊት ግን የተቀባ ብቻ ሳይሆን በሚያጋጥመው ውጊያ ሁሉ የእግዚአብሔርን ድምፅ እየሰማ የሚራመድ ሰው ስለነበረ፣ «ወደ ፍልስጥኤማውያን ልውጣን? በእጄ አሳልፈህ ትሰጣቸዋለህን? ብሎ እግዚአብሔርን ጠየቀ፡፡ እግዚአብሔርም ዳዊትን ፍልስጥኤማውያንን በእርግጥ በእጅህ አሳልፌ እሰጣቸዋለሁና ውጣ አለው» (ቁ. 19)፡፡ ገና ለገና ተቀብተናል ብለን እንደመሰለን መውጣትና መግባት የለብንም፡፡ መቀባት አንድ ነገር ነው፣ ቅባቱ በሕይወታችን እንዲጸናና እንዲያድግ የሚያደርገው ግን የጌታን ድምፅ እየሰማን መመላለሳችን ነው፡፡ ዳዊት በፍልስጥኤማውያን ላይ ድል ካገኘ በኋላ እንደገና ፍልስጥኤማውያን ሊወጉት ሲመጡ እናያለን፡፡ ዳዊትም እንደገና «እግዚአብሔርን ጠየቀ እርሱም፡ - በኋላቸው ዞረህ በሾላው ዛፍ ፊት ለፊት ግጠማቸው እንጂ አትውጣ በሾላውም ዛፍ ራስ ውስጥ የሽውሽውታ ድምፅ ስትሰማ በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር የፍልስጥኤማውያንን ጭፍራ ለመምታት በፊትህ ወጥቶ ይሆናልና በዚያን ጊዜ ቸኩል አለው፡፡ ዳዊትም እግዚአብሔር እንዳዘዘው አደረገ ከገባዖንም እስከ ጌዞር ድረስ ፍልስጥኤማውያንን መታ» (ቁ. 23-25)፡፡

ፍልስጥኤማውያን ሁለተኛ ጊዜ ሲመጡ እነዚህንማ ማሸነፍ እችላለሁ ብሎ ባለፈው ድል ተማምኖ እግዚአብሔርን ሳይጠይቅ ቢወጣ ምናልባት ሳይሸነፍ አይቀርም ነበር፡፡ ዳዊት ግን ባለፈው ልምምዱ ሳይሆን በእያንዳንዱ ውጊያ የእግዚአብሔርን ድምፅ ሳይሰማ መውጣት አልፈለገም፡፡ እግዚአብሔርንም በመጠየቁ እግዚአብሔር አዲስ የሆነ የጦር ስልትን ሲያስተምረው እናያለን፡፡ እኛም ብዙ ጊዜ የተደጋገመ ተመሳሳይ ውጊያ ሲገጥመን ባለፈው ጊዜ ድል ስላገኘሁ ይህንን ውጊያ በራሴ ልወጣው እችላለሁ የሚል ስሜት መጥቶብን

እግዚአብሔርን ከመጠየቅ ወደ ኋላ እንዳንል መጠንቀቅ አለብን፡፡ «ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም» ብሎ አንድ ጊዜ ስለነገረን ሁልጊዜ በእርሱ ላይ መታመንና መደገፍ አለብን፡፡ (ዮሐ. 15፥5)

የዳዊት ምስጢር ሁልጊዜ እግዚአብሔርን መጠየቁ እና <u>እግዚአብሔር እንዳዘዘው</u> ማድረጉ ነበር፡፡

## ምዕራፍ ስድስት

የእግዚአብሔር ታቦት ከአሚናዳብ ቤት ወደ ዳዊት ከተማ እንዴት እንደገባና ዳዊት በእግዚአብሔር ፊት ራሱን ዝቅ አድርጎ እንዳሸበሸበ፦ እንዲሁም በሚስቱ በሳዖል ልጅ በሚልኮል እንደተናቀ እናነባለን፡፡

በ1ሳሙ. 7፥1 ላይ የእግዚአብሔር ታቦት በአሚናዳብ ቤት እንደተቀመጠ የሚናገረውን ክፍል ካየን በኋላ እንደገና ስለ ታቦት የምናነበው በ2ኛ ሳሙ. ምዕራፍ 6 ነው፡፡ በእነዚህ በሁለት ክፍሎች መካከል ቢያንስ ወደ 70 ዓመታት ያህል ይኖራል፡፡ ታቦቱ ወደ አሚናዳብ ቤት የገባው ገና እስራኤላውያን ንጉሥ አንግሥልን ብለው ሳሙኤልን ከመጠየቃቸው 20 ዓመታት በፊት ነበር 1ሳሙ. 7፥2፡፡ ከዚያ በኋላ ሳዖል ነግሦ 40 ዓመታት ከገዛ በኋላ ሲሞት፣ እንዲሁም ዳዊት በኬብሮን ለ7 ዓመታት ነግሦአል፡፡ ሲነግሥ እናያለን፡፡ ከዚያም ዳዊት በእስራኤል ሁሉ ላይ ነግሦ ቢያንስ ሦስት ጦርነቶችን እንደተዋጋ በምዕራፍ 5 አንብበናል፡፡ ይህንን ሁሉ ስናይ ታቦቱ በአሚናዳብ ቤት 70 ዓመታት ያህል እንደኖረ ማስተዋል እንችላለን፡፡ ይህንን ያህል ዓመት የእግዚአብሔር ታቦት ማደሪያ መሆን እንዴት መታደል ነው፡፡

ቀጥሎ የምናነበው ሁኔታ ግን በጣም የሚያሳዝን ነው፡፡ ዳዊት ታቦቱን ከአሚናዳብ ቤት ወደ ዳዊት ከተማ ሊያወጣው ሲል፣ «ወደ ናኮንም አውድማ በደረሱ ጊዜ በሬዎቹ ይፋንኑ ነበርና ዖዛ እጁን ዘርግቶ የእግዚአብሔርን ታቦት ያዘ፡፡ የእግዚአብሔርም ቁጣ በዖዛ ላይ ነደደ፣ እግዚአብሔርም ስለ ድፍረቱ በዚያው ቀሠፈው» ዖዛ፣ የአሚዳብ ልጅ ነበረ፡፡ ዖዛ የእግዚአብሔርን ታቦት እንደቀላል ነገር አይቶት ይሆን? ዕድሜውን ሁሉ ከሕፃንነቱ ጀምሮ በቤታቸው ውስጥ ያየው የነበረ ነገር ስለነበረ የቤተሰብ ቅርስ እንደሆነ አድርጎ አይቶ ይሆን? የዖዛ ድፍረት ከየት እንደመጣ ባናውቅም የእግዚአብሔርን ታቦት እንደማንኛውም ዕቃ ሊያስተካክል ሲሞክር እናያለን፡፡ ብዙ ጊዜ እኛ ክርስቲያኖችም ለብዙ ዓመታት የእግዚአብሔርን ነገር እንላመድና ወደ አጉል ድፍረት ልንሄድ እንችላለን፡፡ የእግዚአብሔር ቤት የጸሎት ቤት መሆን ሲገባው የጥልና የክርክር ቤት ሲሆን የሚታየው፣ ባሪያ ከጌታው ጋር የተላመደ ሲመስለው ነው፡፡ የእግዚአብሔር ቃል፤ «አትሣቱ እግዚአብሔር አይዘበትበትም፤ ሰው ሁሉ የዘራውን ያንኑ ደግሞ ያጭዳልና፡፡» በማለት ከድፍረት ኀጢአት እንድንጠበቅ ያስጠነቀቀናል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ብዙ ጊዜ በእግዚአብሔር ቤት አካባቢ ከልጅነታቸው ጀምሮ ያደጉ ልጆች የእግዚአብሔርን ነገር ከወላጆቻቸው በውርስ ያገኙት ይመስል በእግዚአብሔር ነገር ላይ አውቃለሁ የሚል አጉል ድፍረት ሊኖር ይችላል፡፡ ዳዊት የዖዛን መቀሰፍ ሲያይ፤ «ዳዊት እግዚአብሔርን ፈራና፡ - የእግዚአብሔር ታቦት ወደ እኔ እንዴት ይመጣል? አለ» (ቁ. 8-9)፡፡ ዳዊትም ስለፈራ ታቦቱን በአቢዳራ ቤት አገባው፤ «እግዚአብሔርም አቢዳራንና ቤቱን ባረከ፡፡» እግዚአብሔር ለእርሱ የምናደርገው ነገር ሁሉ በፍርሃትና በአክብሮት እንዲሆን ይፈልጋል፡፡

«ንጉሥ ዳዊትም እግዚአብሔር የአቢዳራን ቤትና የነበረውን ሁሉ ስለ እግዚአብሔር ታቦት እንደባረከ ሰማ፡፡ ዳዊትም ሄዶ የእግዚአብሔርን ታቦት ከአቢዳራ ቤት ወደ ዳዊት

ከተማ በደስታ አመጣው።» (ቁ. 12) የእግዚአብሔርን ነገር በፍርሃትና በአክብሮት ብቻ ሳይሆን በደስታም ማድረግ አለብን። በልባችን ኀዘን እየተሰማን ማድረግ የለብንም። «ዳዊትም በሙሉ ኃይሉ በእግዚአብሔር ፊት ይዘፍን ነበር። ... የሳዖል ልጅ ሜልኮል በመስኮት ሆና ተመለከተች፣ ንጉሡም ዳዊት በእግዚአብሔር ፊት ሲዘልልና ሲዘፍን አየች በልብዋም ናቀችው።» በሰው ዘንድ ከብሮ በእግዚአብሔር ዘንድ ከመናቅ በሰው ዘንድ ተንቆ በእግዚአብሔር ፊት መክበር ይሻላል። ዳዊት ለሜልኮል የነበረው መልስ፡ - «በእግዚአብሔር ፊት ዘፍኛለሁ በእግዚአብሔር ሕዝብ በእስራኤል ላይ አለቃ እሆን ዘንድ ከአባትሽና ከቤቱ ሁሉ ይልቅ የመረጠኝ እግዚአብሔር የተባረከ ይሁን፤ ስለዚህም በእግዚአብሔር ፊት እጫወታለሁ። አሁንም ከሆንሁት በላይ የተናቅሁ እሆናለሁ።» ዳዊት ከሰው ክብር ይልቅ የእግዚአብሔርን ክብር የሚፈልግ ሰው ነበር።

ሜልኮል ግን የእግዚአብሔርን በረከት ትታ እርግማን ስትቀበል እናያለን። ዳዊት ታቦቱን ወደ ከተማ ካስገባ በኋላ «ሕዝቡን በሠራዊት ጌታ በእግዚአብሔር ስም መረቀ። ... ዳዊትም ቤተሰቡን ሊመርቅ ተመለሰ።» ዳዊት ወደቤቱ የመጣው ምርቃት ይዞ ነበር። ማልኮል ግን ያንን ምርቃት ከመቀበል ይልቅ ዳዊት ለእግዚአብሔር ክብር ያደረገውን ነገር ስለናቀች እስከሞተችበት ቀን ድረስ ልጅ እንዳልወለደች እናነባለን። የእግዚአብሔርን ነገር እንደሚገባው ካላከበርን እኛም ከበረከት ይልቅ እርግማንን እንዳናስተናግድ እንጠንቀቅ።

## ምዕራፍ ሰባት

ዳዊት ለእግዚአብሔር ታቦት ማረፊያ የሚሆን ቤት ለመሥራት ሲያስብና እግዚአብሔር በነቢዩ ናታን በኩል ሲመልስለት የሚያሳይ ምዕራፍ ነው።

ዳዊት ሁልጊዜ የእግዚአብሔርን ጽድቅና መንግሥት የሚፈልግ ሰው ስለነበረ ከራሱ ምቾት ይልቅ የእግዚአብሔርን ነገር የሚያስቀድም ነበር።

«እንዲህም ሆነ ንጉሡ በቤቱ በተቀመጠ ጊዜ፣ እግዚአብሔር በዙሪያው ካሉት ጠላቶቹ ሁሉ ባሳረፈው ጊዜ፣ ንጉሡ ነቢዩን ናታንን፡- እኔ ከዝግባ በተሠራ ቤት ተቀምጬአለሁ፣ የእግዚአብሔር ታቦት ግን በመጋረጆች ውስጥ እንደ ተቀመጠ እይ አለው።» ዳዊት ዕረፍትና ፋታ ባገኘ ጊዜ የበለጠ ወደ እግዚአብሔር ልቡን ሲያቀና እናያለን። ብዙ ጊዜ ሰዎች መከራና ችግር፣ ውጊያ ሲበዛባቸው ወደ እግዚአብሔር ከጠላቶቻቸው ሲያሳርፋቸው ግን ወደ ራሳቸው ጉዳይ ነው ዘወር የሚሉት። እግዚአብሔር የዳዊትን ልብ አይቶ በነቢዩ በናታን በኩል «በምድር ላይ እንዳሉ እንደ ታላላቆቹ ስም ታላቅ ስም አደርግልሃለሁ ... ቤት እሠራልሃለሁ ... ከወገብህ የሚወጣው እርሱ ለስሜ ቤት ይሠራል።» ብሎ ብዙ ድንቅ የሆነ የበረከትን ቃል ይነግረዋል። ከዚህ ክፍል አንዳንድ ነገሮችን ማስተዋል እንችላለን።

1ኛ እግዚአብሔር ራሱ ስማችንን ታላቅ ያድርገው እንጂ እኛ ስማችንን ታላቅ ለማድረግ መሞከር እንደሌለብን። በዘፍ. 11÷4 ላይ የባቢሎንን ግንብ የገነቡ ሰዎች ችግር ይህ ነበር። ግንቡን የሠሩበት ዋና ምክንያት «ስማቸውን ለማስጠራት» ነበር።

2ኛ እግዚአብሔር የእኛን ቤት ሕይወት ሳይሠራ እኛ የእሱን ቤት መሥራት እንደማንችል።

3ኛ እግዚአብሔር በእኛ (የሕይወት) ዘመን እንድንሠራ የሚፈልገውን ወይም ያቀደልንን ብቻ እንጂ ከዚያ አልፈን እግዚአብሔር ለሌላ ዘመንና ለሌላ ሰው ያቀደውን ነገር መሥራት እንደማንችል እንማራለን። በሐዋ 13÷36 «ዳዊትም <u>በራሱ ዘመን</u> የእግዚአብሔርን አሳብ

ካገለገለ በኋላ አንቀላፋ።» ይለናል። ከዘመናችን አልፈን የእግዚአብሔርን አሳብ ማገልገል አንችልም።

እግዚአብሔር ለዳዊት ከመለሰለት በኋላ ዳዊት በእግዚአብሔር ፊት ተቀምጦ እግዚአብሔርን ሲባርክና ሲያመሰግን እናያለን።

## ምዕራፍ ስምንት

በዚህ ምዕራፍ ዳዊት በሄደበት ቦታ ሁሉ ጠላቶቹን ድል ሲነሣ እናያለን።

ቁ. 7 «... እግዚአብሔርም ለዳዊት በሄደበት ሁሉ ድልን ሰጠው።»

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ያለውን የዳዊትን ድል በድል መሆን ስናይ ሚስጥሩ በምዕራፍ 7 ላይ ያየነው ዳዊት ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙነት ነው። በእግዚአብሔር ፊት ራሳችንን ሳንጥልና እርሱን ደስ ሳናሰኝ በጠላቶቻችን ላይ ድልን ማግኘት አንችልም። በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ፊት ያልተንበረከከ በጠላቶቹ ፊት መቆም አይችልም።

## ምዕራፍ ዘጠኝ :- በዚህ ምዕራፍ ዳዊት ስለ ዮናታን ውለታ የዮናታን ልጅ ለነበረው ለሜምፊቦስቴ ቸርነት ሲያደርግለት እናያለን።

ሜምፊቦስቴን በምናይበት ጊዜ በምዕ. 4÷4 ላይ እንደተመለከትነው ሞግዚቱ ስትሸሽ ወድቆ በሕፃንነቱ ሽባ የሆነ ልጅ ነው። ሽባ የሆነ ሰው በማንኛውም ኅብረተሰብ እንደ ሙሉ ሰው የሚታይ አይደለም፤ ነገር ግን ዳዊት ስለ ዮናታን ውለታና ቃልኪዳን ሲል ከልጆቹ እኩል ሲያከብረውና ከንጉሥ ገበታ እንዲበላ ሲያደርገው እናያለን። በተጨማሪም የአባቱን ቤት የሳዖልን ርስት ሁሉ ይመልስለታል።

«ንጉሥም የሳዖልን ባሪያ ሲባን ጠርቶ: - ለሳዖልና ለቤቱ ሁሉ የነበረውን ሁሉ ለጌታህ ልጅ ሰጥቻለሁ። አንተና ልጆችህ ሎሌዎችህም ምድሩን እረሱለት ... የጌታ ልጅ ሜምፊቦስቴ ግን ሁልጊዜ ከገበታዬ ይበላል አለው። ... ሜምፊቦስቴም ከንጉሡ ልጆች እንደ አንዱ ከዳዊት ገበታ ይበላ ነበር። ... <u>ሁለት እግሩም ሽባ ነበረ</u>።»

ይህንን ታሪክ ስናይ እግዚአብሔር ስለ ልጁ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲል ለእኛ ለኃጢአተኞች ያደረገውን ቸርነት ያሳየናል ኤፌ. 2÷3-7። «እኛ ሁላችን ደግሞ የሥጋችንንና የልቡናችንን ፈቃድ እያደረግን፣ በሥጋችን ምኞት በፊት እንኖር ነበርን፤ ነገር ግን እግዚአብሔር። ከፍጥረታችን የቁጣ ልጆች ነበርን፤ በምሕረቱ ባለጠጋ ስለሆነ ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሰጠን፣ በጸጋ ድናችኋልና በሚመጡ ዘመናትም በክርስቶስ ኢየሱስ ለእኛ ባለው ቸርነት ከሁሉ የሚበልጠውን የጸጋውን ባለጠግነት ያሳይ ዘንድ ከእርሱ ጋር አስነሣን <u>በክርስቶስ ኢየሱስም በሰማያዊ ስፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን</u>።»

## ምዕራፍ አሥር

ዳዊት በአሞን ልጆችና በሶርያውያን ላይ ድልን ሲያገኝ እናያለን።

የአሞን ልጆች የሎጥ ዝርያዎች ናቸው (ዘፍ. 19÷38)። የአሞን ንጉሥ ሞቶ ልጁ ሐኖን በፋንታው በነገሠ ጊዜ የሐኖን አባት ለዳዊት ወረታ አድርጎለት ስለነበረ፤ (ወረታው ምን እንደሆነ የእግዚአብሔር ቃል አይገልጽልንም) ለልጁ ለሐኖን ቸርነት አደርጋለሁ ብሎ መልእክተኞችን ወደ ሐኖን ይልካል፤ የሐኖንም አማካሪዎች ነገሩን አጣመው «ዳዊት አባትህን

አክብሮ ሊያጽናናህ ባሪያዎቹን የላከ ይመስልሃልን? ዳዊትስ ከተማይቱን ለመመርመርና ለመሰለል ለማጥፋትም ባሪያዎቹን የላከ አይደለምን?» በማለት ክፉ ምክር ይመክሩትና ሐኖን የዳዊትን ባሪያዎች ወስዶ የጢማቸውን ገሚስ በመላጨትና ልብሳቸውን በመቅደድ አሳፍሮ ይሰድዳቸዋል:: ዳዊት በቅንነት ያሰበውን አጣመው ስለተረጎሙት በመካከላቸው ጦርነት ሲነሣ እናያለን:: ከዚህ ታሪክ የምንማረው፤ አንድ ሰው ኅሊናውና አስተሳሰቡ ጠማማ ከሆነ መልካም ነገር ቢመጣለትና ቢደረግለት እንኳን የሚያየውና የሚተርጉመው በተጣመመ አመለካከት እንደሆነ ነው:: «ሁሉ ለንጹሖች ንጹሕ ነው፤ ለርኩሳንና ለማያምኑ ግን ንጹሕ የሆነ ምንም የለም፣ ነገር ግን አእምሮአቸውም ኅሊናቸውም ረክሶአል::» ቲቶ 1÷15

ብዙ ጊዜ አመለካከታችንና ኅሊናችን ቀና በማይሆንበት ጊዜ አንድ ሰው አንድ ነገር ሲያደርግ ወይም ሲናገር ቶሎ ብለን አጣምመን እንተረጉመውና ሰውዬውን እንቀየማለን ወይም እንርቃለን:: ያ ሰው ግን ያደረገውን ነገር ያደረገው በቅንነት፣ በየዋህነት ወይም ባለማስተዋል ሊሆን ይችላል:: እርሱ ባላወቀው ነገር ተቀይመነውና ጠልተነው እንኖራለን:: እግዚአብሔር ከእንደዚህ ዓይነት ጠማማ አመለካከት ይጠብቀን:: «የሰውነት መብራት ዐይን ናት:: ዐይንህ እንግዲህ ጤናማ ብትሆን ሰውነትህ ሁሉ ብሩህ ይሆናል፣ ዐይንህ ግን ታማሚ ብትሆን ሰውነትህን ሁሉ የጨለመ ይሆናል (ማቴ. 6÷22-23):: በዚህ ጥቅስ ላይ ዓይን የሚለው በአጠ ቃላይ አመለካከታችንን እንጂ ስለ ሥጋዊ ዐይናችን አይደለም:: የሥጋዊ ዐይናችን ምድራዊውን ብርሃን እንድናይ እንደሚረዳን ሁሉ ዐይነ ልቦናችን ጤናማ ሲሆን ደግሞ ሕይወታችን በብርሃን እንደሚሞላ ማወዳደሩ ነው::

በዚህ ሁኔታ በተነሣው ጦርነት የአሞን ልጆች ሶርያውያንን ቀጥረው እስራኤልን በሁለት ግንባር ሲዋጉ እናያለን:: «ኢዮአብም በፊትና በኋላ ሰልፍ እንደከበበው ባየ ጊዜ ከእስራኤል ምርጥ ምርጦቹን ሁሉ መረጠ፣ በሶርያውያንም ፊት ለሰልፍ አኖራቸው:: የቀረውንም ሕዝብ በወንድሙ በአቢሳ እጅ አድርጎ በአሞን ልጆች ፊት ለሰልፍ አኖራቸው::» ቁ. 9-10:: ከእነዚህ ጥቅሶች የምንማረው፤ አንዳንድ ጊዜ ጠላት በአንድ በኩል ብቻ ሳይሆን በሁለት በኩል ወይም ዙሪያችንን የሚከበን ጊዜ አለ:: አንድ ሰው በአንድ ጊዜ መዋጋት የሚችለው በአንድ ግንባር ብቻ ስለሆነ በሌሎቹ ግንባሮች የሚዋጉልን ወንድሞች እንደሚያስፈልጉን ያሳየናል:: ኢዮአብ በሁለቱም ግንባር በአንድ ጊዜ መዋጋት ስለማይችል ወንድሙን አቢሳን በአንደኛው ግንባር ሲያሰልፈው እናያለን:: በአንጻሩም፤ አንዳንድ ወገኖቻችን የጠላት ውጊያ ዙሪያቸውን ከብቦአቸው ስናይ ልንዋጋላቸው እንደሚገባን ያስተምረናል::

ኢዮአብም አቢሳን፤ «አይዞህ ስለ ሕዝባችንና ስለ አምላካችን ከተሞች እንበርታ እግዚአብሔርም ደስ ያሰኘውን ያድርግ አለ::» የምንዋጋው ለራሳችን ብቻ ሳይሆን ለወገኖቻችንና ለአምላካችን ነው:: የእግዚአብሔር ሕዝብ እየተረዳዳ በሚዋጋበት ጊዜ ጠላታችን ይሸነፋል:: «ለአድርአዛርም የሚገብሩ ነገሥታት ሁሉ በእስራኤል ፊት እንደ ተሸነፉ ባዩ ጊዜ ከእስራኤል ጋር ታረቁ ገበሩላቸውም::»

## ክፍል 2 የዳዊት ኀጢአትና ውድቀት ምዕ. 11-24

### *ምዕራፍ አሥራ አንድ*

*ይህ ምዕራፍ የዳዊት ኃጢአትና ውድቀት የጀመረበት ምዕራፍ ነው:: በዚህ ምዕራፍ የምናየው ውሃ ሲወስድ እያሳሳቀ ነው እንደሚባለው፣ ዳዊት እንዴት ከአንድ ኃጢአት ወደ ሌላው እየተላለፈ እንደሄደ ነው::*

ይህ ምዕራፍ የሚጀምረው፤ «እንዲህም ሆነ በዓመቱ መለወጫ ነገሥታት ወደ ሰልፍ በሚወጡበት ጊዜ ዳዊት ኢዮአብን ከእርሱም ጋር ባሪያዎቹን እስራኤልንም ሁሉ ሰደደ። የአሞንም ልጆች አገር አጠፉ፣ ረባትንም ከበቡ፤ ዳዊት ግን በኢየሩሳሌም ቀርቶ ነበር» በማለት ነው። ከዚህ ጥቅስ እንደምናነበው፣ የዳዊት ውድቀት መንስኤው ከሠራዊቱ ጋር ወጥቶ መዋጋት ሲገባው በኢየሩሳሌም መቅረቱ እንደሆነ እናያለን። የዳዊት ቅባት የውጊያ ቅባት ነው። እግዚአብሔርም ያነገሠው የእስራኤልን ጠላት ተዋግቶ እስራኤልን እንዲታደግና እንዲጠብቅ ነው። በምዕ. 8 ላይ «እግዚአብሔርም ዳዊት <u>በሄደበት</u> ሁሉ ድልን ሰጠው።» የሚል ቃል አይተን ነበር። እግዚአብሔር ድልን የሚሰጠን ሄደን ስንዋጋ እንጂ እጃችንን አጣምረን በቤት ቁጭ ስንል አይደለም። በተለይ የዓመቱ መለወጫ «ነገሥታት ወደ ሰልፍ በሚወጡበት ጊዜ» ዳዊት ንጉሥ ሆኖ በዚያን ጊዜ ለሰልፍ አለመውጣቱ እንደተዝናና ያሳየናል። የእግዚአብሔር ሰዎች ሆነን ሰልፍ እየተፋፋመ መዝናናት አንችልም ዳዊት በቤቱ ቁጭ ብሎ ኢዮአብን ሲልክ ይህ ሁለተኛው ጊዜ እንደሆነ እናያለን። በምዕ. 9÷7 የአሞንን ልጆች እንዲዋጋ ኢዮአብን ሲልክ እናያለን። ከዚህ ሁኔታ የምንማረው አብዛኛውን ጊዜ የኃጢአታችን ጅማሬ የአለማድረግ ኀጢአት /Sin of Omission/ እንደሆነ ነው። «እንግዲህ በጎ ለማድረግ አውቆ ለማይሠራው ኀጢአት ነው» ያዕ. 4÷17። ማድረግ ያለብንን በጎ ነገር በማናደርግበት ጊዜ ማድረግ የሌለብንን ለማድረግ የተጋለጥን እንሆናለን። ጠላትም ያንን ዕድል ተጠቅሞ በኀጢአት እንድንወድቅ ወጥመድን ያዘጋጅልናል።

በዳዊት ሕይወት የተፈጸመው ይህ ትዕይንት ነበር። ጠላት የእግዚአብሔርን ሕዝብና አገር ሲያጠፉ ዳዊት በቤተ መንግሥቱ ተመችቶት ተቀምጦ ነበር። «የአሞን ልጆች አገር አጠፉ፣ ረባትንም ከበቡ ዳዊት ግን በኢየሩሳሌም ቀርቶ ነበር» 2ሳሙ 11÷1።

በዚህ ሁኔታ ሳለ ጠላት አነሳስቶ ወደ ወጥመድ ሲያገባውና በጠላት ወጥመድ ሲያዝ ከዚያም ለማምለጥ ብዙ ሲጥርና በኃጢአት ላይ ኃጢአትን ሲጨምር እናያለን።

«እንዲህም ሆነ ወደ ማታ ጊዜ ዳዊት ከምንጣፉ ተነሣ፣ በንጉሥም ቤት በሰገነት ላይ ተመላለሰ፣ በሰገነቱ ሳለ አንዲት ሴት ስትታጠብ አየ፤ ሴቲቱም መልከ መልካም ነበረች። ... ዳዊትም ልኮ አስመጣት ወደ እርሱም ገባች፤ ... ከእርስዋም ጋር ተኛ ወደ ቤትዋም ተመለሰች» ቁ. 2-4። በዚህ ትዕይንት ውስጥ ብዙ ነገሮችን እናያለን። ዳዊት ከጅምሩ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ ስለነበረ ወደ ሰልፍ ባለመውጣቱ ጠላት አነሳስቶ ወደ ፈተናና ወጥመድ ሲያስገባው እናያለን።

«ከምንጣፉ ተነሣ ....
አንዲት ሴት ስትታጠብ አየ ...
መልእክተኞች ልኮ አስመጣት ...
ከእርስዋ ጋር ተኛ... »

የሰይጣንንና የሥጋችንን አብሮ መሥራት በተግባር የምናይበት ክፍል ነው። ሰይጣን አነሣስቶ ወደ ፈተና ሲመራው በአንፃሩ ደግሞ እዚያ ማዶ ለዓይኑ የሚያስጐመጅን ወጥመድ ሲያዘጋጅለት እናያለን። ከሔዋን ጀምሮ ሰይጣን በዐይን አምሮት ወይም መጎምጀት ብዙዎችን በኃጢአት ሲፈትንና ሲጥል እናያለን። «ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም <u>የሥጋ ምኞትና</u> <u>የዐይን አምሮት</u> <u>ስለ ገንዘብም መመካት</u> ... ስለሆነ» 1ዮሐ. 2÷15።

«ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ይፈተናል። ከዚህ በኋላ ምኞት ፀንሳ ኃጢአትን ትወልዳለች፣ ኃጢአትም ካደገች በኋላ ሞትን ትወልዳለች» ያዕ. 1÷14-15።

«ሴቲቱም (ቁ. 5)፡፡ በስውር የተሠራ ኃጢአት ምንም ቢሸፋፈን መውጣቱ እንደማይቀር እናያለን፡፡ ዳዊትም እንደ አረገዘች ሲሰማ ኦርዮን የተባለውን ከእስራኤል ስመ-ጥር ከነበሩት ጀግኖች አንዱ የነበረውን ባልዋን 2ሳሙ. 23፥39 ጠርቶ ያስመጣውና ወደ ቤትህ ሂድ ብሎ ከእርሱ ሳይሆን ከባልዋ ያረገዘች እንዲመስል ነገሩን ለመሸፋፈን ይሞክራል፡፡ «ኃጢአቱን የሚሠውር አይለማም፤ የሚናዘዘባትና የሚተዋት ግን ምሕረትን ያገኛል» (ምሳሌ 28፥13)፡፡ በዳዊት ሕይወት ከመጀመሪያው ኃጢአቱ ይልቅ ኃጢአቱን ለመሠወር ያደረገው የከፋ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

በአጠቃላይ ምዕራፉን ስናይ ዳዊት ኃጢአቱን ለመሠወር ኦርዮንን ሲሸንግል፣ ሲያሰክር፣ በመጨረሻም ሲያስገድል እናያለን፡፡ «የኦርዮንም ሚስት ባልዋ ኦርዮን እንደሞተ በሰማች ጊዜ ለባልዋ አለቀሰች፡፡ ... ዳዊትም ልኮ ወደ ቤቱ አስመጣት፣ ሚስትም ሆነችው ወንድ ልጅም ወለደችለት፤ ነገር ግን ዳዊት ያደረገው ነገር ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሆነ፡፡» በዳዊት ቤት፣ ሁሉ ነገር ተሸፋፍኖ ያለፈለትና አገር ጤና የሆነ መስሎት ነበር፡፡

ዳዊት በዚህ ምዕራፍ ያደረጋቸውን ነገሮች በአጠቃላይ እንመልከት፤

1. ወጥቶ መዋጋት ሲገባው በኢየሩሳሌም ቀረ
2. ክፉ የዐይን አምሮትና ምኞትን ተመኘ
3. አመነዘረ
4. ኦርዮንን ሸነገለ
5. አሰከረው (ዕንባቆም 2፥15)
6. አስገደለው
7. የእግዚአብሔርን ስም የሚያሰድብ ነገር ምዕ. 12፥14

ከዚህ ምዕራፍ ሌላ ሳንጠይቅ ማለፍ የሌለብን ነገር ስለ ኦርዮን ሚስት ስለ ቤርሳቤህ ነው፡፡ እርስዋም እንደማንኛውም እስራኤላዊ የሙሴን ሕግ አሥርቱ ቃላትን የምታውቅ ስለነበረች ምንም እንኳን የአገሩ ንጉሥ ቢጠይቃትም የነገሥታት ንጉሥ የሆነውን የእስራኤልን አምላክ ትእዛዝ መተላለፍ የለባትም ነበር፡፡ ቤርሳቤህ የእምነት ሴት ሆና ንጉሡን፣ «ይህ መተላለፍ ከንጉሡ ይራቅ፤ ይህንን ኀጢአት አላደርግም» ብትል ኖሮ ምናልባት ንጉሡን ሊወድቅበት ከነበረው ኀጢአት ልትጠብቀው ትችል ነበረ፡፡ አዳም እግዚአብሔርን «ከእኔ ጋር እንድትሆን የሰጠኸኝ ሴት እርስዋ ከዛፉ ሰጠችኝና በላሁ፡፡» ብሎ ማሳበቡ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት አለማግኘቱ የሚያሳየን ቤርሳቤህም በንጉሡ ማመካኘት እንደማትችል፤ ሁሉ በተናጠል በእግዚአብሔር ፊት ተጠያቂና ኃላፊነት ያለበት እንደሆነ ነው፡፡ የአንዱ መተላለፍ ከሌላው ጎልቶ ሊታይ ይችላል፤ ነገር ግን የአንዱ መተላለፍ የሌላውን ተጠያቂነት አያስወግድም፡፡

ቁ. 4 ላይ «ዳዊትም መልእክተኞች ልኮ አስመጣት፤ ወደ እርሱም ገባች» የሚል ቃል እናነባለን፡፡ «ከእርሱም ጋር ገባች» የሚለው ቃል የእርስዋን በፈቃድዋ በዚህ ኃጢአት መተባበር ያሳያል፡፡

ምዕ. 12 ይህ ምዕራፍ እግዚአብሔር በነቢዩ በናታን በኩል ዳዊትን ሲገስጸው የሚያሳይ ክፍል ነው፡፡

ነቢዩ ናታን እግዚአብሔር የሰጠውን መልእክት፣ መልካምም ሆነ ክፉ ነገር በተመለከተ በቀጥታ የሚያስተላልፍ ነቢይ ነበር፡፡ ከዳዊት ጋር የጓደኝነትም ዐይነት ግንኙነት እንደነበራቸው ከምዕ 7 ተመልክተናል፡፡ በምዕ 7 ናታን ለዳዊት ልዩ የሆነ ክብርና ሞገስ የተሞላበትን መልእክት ከእግዚአብሔር ሲያመጣለት እናያለን፡፡ በምዕ 12 ግን የተግሣጹንና

የቅጣትን መልእክት ነበር ከእግዚአብሔር የተቀበለው። ዳዊት እኮ እንደ ጓደኛዬ ነው ይህንን ከባድ የተግሣጽ መልእክት እንዴት አስተላልፋለሁ ብሎ አላመነታም። እውነተኛ ነቢይ እግዚአብሔር የሚሰጠውን መልእክት ሳይጨምርና ሳይቀንስ ወይም ሳያሻሽል የሚያስተላልፍ እንደሆነ እናያለን።

ነቢዩ ናታን ለዳዊት ያስተላለፈው መልእክት በምሳሌ መልክ እንደነበረ እናያለን። ያም ምሳሌ በአንድ ባለጠጋና ድሃ መሐከል የተከሰተ ትእይንት ነበረ። ባለጠጋው ሰው ለራሱ በጎች ሳስቶ የድሃውን አንዲት በግ ነጥቆ ለመጣበት እንግዳ ምግብ እንዳዘጋጀለት ለዳዊት ይነግረዋል። ዳዊት ግን የማን ታሪክ መሆኑን ሳያውቅ በመንግሥቴ እንዲህ ያለ ነገር እንዴት ይደረጋል ብሎ ሲፈርድ እናያለን።

ቁ. 7 «ናታንም ዳዊትን፦ ያሰው አንተ ነህ።» ይለዋል። ከዚህ ትዕይንት የምንማረው፤ በሌሎች ላይ መፍረድ ቀላል እንደሆነና፣ በሌሎች ላይ በፈረድን ቁጥር በራሳችንም ላይ እየፈረድን እንደሆነ ነው።

ሮሜ 2፥1 «ስለዚህ አንተ የምትፈርድ ሰው ሁሉ ሆይ፣ የምታመካኘው የለህም፣ በሌላው በምትፈርድበት ነገር ራስህን ትኰንናለህና፤ አንተው ፈራጁ እነዚያን ታደርጋለህና»? በአንፃሩ ደግሞ የእግዚአብሔር ፍርድ ምን ያህል ቅን እንደሆነ እናያለን። እግዚአብሔር በእኛ ላይ የሚፈርደው የገዛ ኀጢአታችንን እንኳን ምሥክር አድርጎ እንደሆነ ያስተምረናል። የገዛ ኀጢአታችን «እግዚአብሔር ሆይ ፍርድህ የሚገባኝ ነው፤ እንደውም ከሚገባኝ ያነሰ ነው» ብሎ የሚቀበለው ፍርድ ነው።

ዳዊት የናታንን መልእክት ከሰማ በኋላ፤ «ዳዊትም ናታንን ፦ እግዚአብሔርን በድያለሁ አለው» ቁ. 13። የሚል ቃል እናነባለን። በ1ሳሙ. 15፥19-20 ያለውን ነቢዩ ሳሙኤል ሳዖልን ሲገስጸው የመለሰውን መልስ ከዳዊት መልስ ጋር ስናወዳድር የዳዊትንና የሳዖልን ልብ ልዩነት ማየት እንችላለን። ሳዖል በመጀመሪያ ከአንደበቱ የወጣው መልስ፤ «ሳዖልም ሳሙኤልን፡ - የእግዚአብሔርን ቃል ሰምቻለሁ እግዚአብሔርም በላከኝ መንገድ ሄጃለሁ።» የሚል በደልን ያለ መቀበል መልስ ነበረ። ዳዊት ግን «እግዚአብሔርን በድያለሁ» አለ። ሁለቱም በእግዚአብሔር ፊት ክፉ የሆነን ነገር ነበር ያደረጉት። ልዩነታቸው የእግዚአብሔርን ተግሣጽ አቀባበላቸው ላይ ነበረ። አንዱ በንሥሐና በተሰበረ ልብ ተቀበለው፤ ሌላው በአመጸኛና በእልከኛ ልብ ተቀበለው። የዳዊትን የንስሐ ልብ የበለጠ የምናየው በመዝ. ምዕ. 50 (51) ነው።

እግዚአብሔርም የዳዊትን ልብ አይቶ በናታን በኩል «እግዚአብሔር ደግሞ ኀጢአትህን አርቆልሃል፣ አትሞትም።» ይለዋል።

የእግዚአብሔር ሰዎች ሆነን የምናደርጋቸው ነገሮች የእግዚአብሔርን ስም ያሰድባሉ ቁ. 14። «ነገር ግን በዚህ ነገር ለእግዚአብሔር ጠላቶች ታላቅ የስድብ ምክንያት አድርገሃልና ስለዚህ የተወለደልህ ልጅ ፈጽሞ ይሞታል አለው።»

ከቁ. 16-23 ዳዊት ስለ ህፃኑ እግዚአብሔርን በጾምና በጸሎት ደጅ ይጠናል። «ዳዊትም ስለ ህፃኑ እግዚአብሔርን ለመነ ዳዊትም ጾመ ገብቶም በመሬት ላይ ተኛ። ... በሰባተኛውም ቀን ሕፃኑ ሞተ።» ከዚህ ጥቅስ የምናየው፤ ዳዊት ምንም እግዚአብሔርን በጾምና በጸሎት ለሰባት ቀን ደጅ ቢጠናም የእግዚአብሔር ውሳኔ እንዳልተለወጠ ነው። አንዳንድ ጊዜ ምንም ዐይነት ጸሎትና ልመና ብናበዛ የማይለወጡ የእግዚአብሔር ውሳኔዎች አሉ። እኛ እነዚያን ውሳኔዎች ለመቀበል መለወጥ አለብን እንጂ የእግዚአብሔር ሐሳብ አይለወጥም። «ዳዊትም ባርያዎቹን፡ - ሕፃኑ ሞቷል? አላቸው። እነርሱም፡ - ሞቷል አሉት። ዳዊትም ከምድር ተነሥቶ ታጠበ፣ ተቀባም፣ ልብሱንም ለወጠ ወደ እግዚአብሔርም ቤት ገብቶ ሰገደ። ወደ ቤቱም መጣ፦

እንጀራ አምጡልኝ አለ፤ በፊቱም አቀረቡለት፣ በላም» (ቁ. 19-20)። የእግዚአብሔር ሐሳብ ስላልተለወጠ ዳዊት ራሱን ከእግዚአብሔር ሐሳብ ጋር ለማስተካከል የራሱን ሐሳብና ሁኔታ ለወጠ። የእግዚአብሔርን ሐሳብ አሜን ብሎ ተቀበለ፣ ሰገደ።

የዚህን ነገር ሚስጥር አስረዳን ብለው ባሪያዎቹ ሲጠይቁት፤ «ሕፃኑ ሕያው ሳለ እግዚአብሔር ይምረኝ ሕፃኑም በሕይወት ይኖር እንደሆነ ማን ያውቃል? ብዬ ጾምሁ አለቀስኩም፣ አሁን ግን ሞቷል የምጾመው ስለምንድር ነው? በውኑ እንግዲህ እመልሰው ዘንድ ይቻለኛልን? እኔ ወደ እርሱ እሄዳለሁ እንጂ እርሱ ወደ እኔ አይመለስም አለ።» ትልቅ ማስተዋል ያለበት መልስ ነው። የምንግልድበትንና የምንጾበትን ምክንያት ማወቅ እንዳለብን ያስተምረናል። «የምጾመው ለምንድነው?» የሚለው ጥያቄ እያንዳንዳችን መጠየቅ ያለብን ጥያቄ ነው። የምንጾምበት ምክንያት ሥርዐትን ለማሟላት ወይም የማይለወጥን ነገር ለመለወጥ መሆን የለበትም። «እኔ ወደ እርሱ እሄዳለሁ እንጂ እርሱ ወደ እኔ አይመለስም» የሚለው ቃል፤ ሕፃናት ሲሞቱ ወደ እግዚአብሔር <u>ወደ መንግሥተ ሰማይ</u> እንደሚሄዱ ያሳየናል።

ከቁ. 26-31 ኢዮአብ ዳዊትን «ረባትን ወግቻለሁ ... አሁንም ከተማይቱን እንዳልይዝ፣ በስሜም እንዳትጠራ፣ የቀረውን ሕዝብ ሰብስብ ከተማይቱንም ከብበህ ያዝ» ብሎ መልእክተኞችን ይልካል። በምዕ. 11÷1 «... የአሞንም ልጆች አገር አጠፉ፣ ረባትንም ከበቡ፤ ዳዊት ግን በኢየሩሳሌም ቀርቶ ነበር።» የሚለውን ጥቅስ ተመልክተን ነበር። ዳዊት ወደ ረባት ወጥቶ መውጋትና መያዝ የነበረበት፣ ከአንድ ዓመት በፊት በኃጢአት ሳይወድቅ ነበር። በምዕ. 11÷1 ያላደረገውን የማይቀርለትን ውጊያ በምዕ. 12÷29 ላይ ሲዋጋ እናያለን። በጊዜው ወደ ውጊያ ቢሄድ ግን ምናልባት ከውድቀትም ይጠበቅ ነበር።

## ምዕራፍ አሥራ ሦስት

ይህ ምዕራፍ እግዚአብሔር በናታን በኩል ለዳዊት «እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ እነሆ ከቤትህ ክፉ ነገር አስነሣብሃለሁ» (ምዕ. 12÷11)። ብሎ የተናገረው ትንቢት ጅማሬ ነው።

አምኖን የሚባለው የዳዊት በኩር ልጅ ግማሽ እህቱ (በአባት ብቻ) የነበረችውን ትዕማርን ስለ ወደዳት በግድ ሲያስነውራትና፣ ሙሉ ወንድሟ የነበረው አቤሴሎም ተበቅሎ ሲያስገድለው እናያለን።

«አምኖንም ከእኅቱ ከትዕማር የተነሣ እጅግ ስለ ተከዘ ታመመ» (ቁ. 2)። ይህ ጥቅስ የሚያሳየን፣ ትካዜ ወይም ጭንቀት የሕመም ዋዜማ ሊሆን እንደሚችል ነው። በእንግሊዝኛ (Psychosomatic) ሕመም ብለው የሚጠሩት ዐይነት ሕመም ነው። ትርጓሜውም ከነፍስ (Psyche) ቀውስ ጋር የተያያዘ የሥጋ ሕመም ማለት ነው። አንድ ሰው ብርድ መትቶት ቢታመም የሥጋ ሕመም ብቻ ነው ማለት እንችላለን። ነገር ግን የአምኖን ሕመም ሥጋዊ ብቻ ሳይሆን ከነፍስ ቀውስ (ትካዜና ጭንቀት) የተነሣ ነበር።

ከቁ. 3-5 አንድ እጅግ ብልህ የሆነ የዳዊት የወንድም ልጅ አምኖንን ክፉ ምክር ሲመክረው እናነባለን። እግዚአብሔር ለበጎ የሰጠንን ማንኛውንም ስጦታ ለክፉ መጠቀም እንደምንችል ያሳስበናል። በመጀመሪያ አምኖንን አንድ ጥያቄ ይጠይቀዋል። «የንጉሥ ልጅ ሆይ ስለምን ቀን በቀን እንዲህ ከሳህ?» ከጥያቄው በኋላ የመጣው ምክር ነው እንጂ ጥያቄው መልካም ጥያቄ ነበረ። የንጉሥ ልጅ ሆነህ፣ የምትፈልገውን ነገር ሁሉ ንጉሡ ሊሰጥህ ሲችል እንዴት እንደዚህ ከሳህ? የሚል ጥያቄ ነው። እኛም ክርስቲያኖች የነገሥታት ንጉሥ የሆነው አምላካችንና አባታችን እያለልን፤ «እርሱ ስለ እናንተ ያስባልና የሚያጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት» (1ጴጥ. 5÷7) ተብለን፤ በብዙ ነገር ስንተክዝና ስንጨነቅ እንገኛለን። መዝ. 55ትን ዳዊት መቼ

እንደጻፈው ባይታወቅም በዚህን ጊዜ ለልጁ ለአምኖን የሚያስፈልገውን ምክር ያዘለ ምዕራፍ ነበር፡፡ «ትካዜህን በእግዚአብሔር ላይ ጣል እርሱም ይደግፍሃል» (መዝ. 55÷22)፡፡

አምኖን ግን እጅግ ስለ ተከዘ ታመመ፡፡ የዳዊት የወንድም ልጅ የነበረው ኢዮናዳብ አምኖንን ክፉ ምክር በመምከር፤ አምኖን፣ እኅቱን ምግብ እንድትሠራለትና እንድታስታምመው ዳዊትን ያስፈቅድና እቤቱ ከመጣች በኋላ አስገድዶ ያስነውራታል፡፡

እኅቱ ትዕማር ግን ይህንን ኃጢአት እንደ ቤርሳቤህ አሜን ብላ አልተቀበለችም፡፡ «እርስዋም መልሳ፡- ወንድሜ ሆይ አይሆንም እንዲህ ያለ ነገር በእስራኤል ዘንድ አይገባምና አታሳፍረኝ፤ ይህንም ነውረኛ ነገር አታድርግ፡፡ እኔም ነውሬን ወዴት ልሸከም? አንተም በእስራኤል ዘንድ ከምናምንቴዎች እንደ አንዱ ትሆናለህ፤ እንግዲህ ለንጉሡ ንገረው እኔንም አይነሳህም፡፡ አለችው፡፡» ትዕማር ነገሩን ከሁሉም አቅጣጫ አመዛዝና እንዳስተዋለች ማየት እንችላለን፡፡ ለእርሱም ለእርስዋም ነውርና ውርደት እንደሚሆን ከነገረችው በኋላ «ለንጉሡ ንገረው እኔንም አይነሣህም» በማለት ትክክለኛው መንገድ በንጉሡ በኩል እንደሆነ ታመለክተዋለች፡፡ እርሱ ግን የራሱን ስሜት መቆጣጠር ስላልቻለ «ቃልዋን አልሰማም ... በግድ አስነወራት ...»

በኃጢአት የሚገኝ ደስታ ጊዜያዊ ነውና (ዕብ. 11÷26)፤ «ከዚያም በኋላ አምኖን ፈጽሞ ጠላት አስቀድሞም ከወደዳት ውድ ይልቅ በኋላ የጠላት ጥል በለጠ፡፡ አምኖንም ተነሥተሽ ሂጂ አላት» (ቁ. 15)፡፡

ከቁ. 20-39 አቤሴሎም በአምኖን ላይ ለሁለት ዓመት ቂም ይዞ ሲያስገድለውና ሲኮበልል እናያለን፡፡

በቁ. 20 ላይ አቤሴሎም ለእህቱ ለትዕማር የሚሰጣት ምክርና በእርሱ በራሱ ልብ የነበረው ሐሳብ ተቃራኒ ነበር፡፡ «ወንድምዋም አቤሴሎም፡- ወንድምሽ አምኖን ከአንቺ ጋር ነበረን? እኅቴ ሆይ፣ አሁን ግን ዝም በዪ ወንድምሽ ነው ይህን ነገር በልብሽ አትያዢ አላት» (ቁ. 20)፡፡ እርሱ ግን ለሁለት ዓመት ሙሉ ቂሙን በልቡ አኑሮ አምኖንን ሲያስገድል እናያለን፡፡

«እንግዲህ አንተ ሌላውን የምታስተምር ራስህን አታስተምርምን?» (ሮሜ 2÷21) አቤሴሎም እኅቱን ትዕማርን የመከረውንና ያስተማረውን ለራሱ ቢጠቀምበት ከብዙ ጥፋት ይጠበቅ ነበር፡፡ ዳዊት ልጆቹን እንደሚገባ የሚገሥጽ አባት እንዳልነበረ ከቁ. 21 እናነባለን፡፡ «ንጉሡም ዳዊት ይህን ነገር በሰማ ጊዜ እጅግ ተቆጣ ነገር ግን የበኩር ልጁ ነበርና ስለወደደው የልጁን የአምኖንን ነፍስ አላሳዘውም፡፡» ምናልባት አቤሴሎም በአምኖን ላይ የተበቀለው ዳዊት አምኖንን ስለሠራው ሥራ እንደሚገባ ስላልገሰጸው ሊሆን ይችላል፡፡

በመጨረሻ፤ አቤሴሎም ኮብልሎ ወደ ጌሹር ንጉሥ ልጅ ይሄዳል፡፡ ይህ የጌሹር ንጉሥ ልጅ የአቤሴሎም አያት (የእናቱ አባት) እንደሆነ በ2ሳሙ. 3÷3 እንረዳለን፡፡

## <u>ምዕራፍ አሥራ አራት</u>

የዳዊት የሠራዊት አለቃ የነበረው ኢዮአብ የዳዊት ልብ አቤሴሎምን እንደናፈቀ ስለተረዳ አንዲትን ሴት በስውር ወደ ንጉሡ አስገብቶ የፈጠራ ታሪክ በአፍዋ አድርጎ ንጉሡ፣ አቤሴሎምን ከተሰደደበት እንዲመልስ ያደርገዋል፡፡ በኢዮአብ አማካኝነት ንጉሥ ዳዊትና ልጁ አቤሴሎም ሲታረቁ እናያለን፡፡

## <u>ምዕራፍ አሥራ አምስት</u>

በዚህ ምዕራፍ፣ አቤሴሎም ከአባቱ ይቅርታን ተቀብሎ ወደ ንጉሥ ከተማ ከገባ በኋላ እንዴት የሕዝቡን ልብ እንደሠረቀና ከአራት ዓመት በኋላ እንዴት በኬብሮን እንደነገሠ፣ እንዲሁም ንጉሥ ዳዊትና ተከታዮቹ ከኢሩሳሌም እንዴት እንደሸሹ እናነባለን።

ከቁ. 1-12 በምናይበት ጊዜ አቤሴሎም ቀስ በቀስ የእስራኤልን ሕዝብ ልብ እንዴት እንደሠረቀ እናያለን። «አቤሴሎም በማለዳ ተነሥቶ በበሩ አደባባይ ይቆም ነበር፤ አቤሴሎምም ከንጉሥ ለማስፈረድ ጉዳይ የነበረውን ሁሉ ወደ እርሱ እየጠራ... ነገርህ እውነትና ቅን ነው ነገር ግን ከንጉሥ ታዝዞ የሚሰማህ የለም፤ ይለው ነበር። አቤሴሎምም፦ ነገርና ክርክር ያለው ሁሉ ወደ እኔ ይመጣ ዘንድ ቅንም ፍርድ እፈርድለት ዘንድ በአገር ላይ ፈራጅ አድርጎ ማን በሾመኝ ይል ነበር። ሰውም እጅ ሊነሣው ወደ እርሱ በቀረበ ጊዜ እጁን ዘርግቶ ይይዝና ይስመው ነበር።» ጠላት በመጀመሪያ የሚገለጸው መልካም መስሎ ነው። በውጭ የሚታየውን መልካም የሚመስል ነገር ሳይሆን ከጀርባው ያለውን ክፉ መንፈስ ማየት አለብን።

«የተጠሩትም ሁለት መቶ ሰዎች ከአቤሴሎም ጋር በየዋህነት ከኢየሩሳሌም ሄዱ <u>የሚሆነውንም ነገር ከቶ አያውቁም ነበር</u>።» እንደ አቤሴሎም ያሉ ውስጥ ለውስጥ ክፋትን የሚሠሩ ሰዎችን የሚከተሉ ሰዎች ብዙውን ጊዜ የዋሆችና አላዋቂዎች እንደሆኑ እናያለን።

ይህ ሁሉ ዓመጽና የዳዊት ከመንግሥቱ ተፈናቅሎ መሰደድ እግዚአብሔር በናታን በኩል ለዳዊት የተናገረው ቅጣት የሚፈጸምበት መንገድ ነበር። አቤሴሎም በቁ. 4 ላይ «ማን በሾመኝ» እያለ ለሥልጣን የነበረውን ጥማት ሲገልጽ፣ ዳዊት ግን ጥማቱ ሥልጣን ስላልነበረ፣ ታቦቱ ከእኔ ጋር አይሰደድም እግዚአብሔር የወደደውን ያድርግብኝ ብሎ «ተከናንቦ ያለ ጫማ እያለቀሰ ወደ ደብረ ዘይት ዐቀበት ወጣ።» ዳዊት ይህ ሁሉ የሆነው ስለ ኃጢአቱ ቅጣት እንደሆነ ስለተረዳ የእግዚአብሔርን ታቦት ከእርሱ ጋር ማንከራተት አልፈለገም።

ዳዊት በዚህ ዐይነት የጉስቁልና ሁኔታ ውስጥ ሆኖ እንኳን ሳያማርር ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይ እናያለን። «ዳዊትም፦ አቤቱ የአኪጦፌልን ምክር ስንፍና አድርገህ እንድትለውጥ እለምንሃለሁ አለ» (ቁ. 31)። አኪጦፌል የሚባለው ሰው ምክር ከባድ ምክር እንደሆነ ስለሚያውቅ ከአኪጦፌል ምክር እግዚአብሔር እንዲጠብቀው ይለምናል። ወዲያውኑ የጸሎቱ መልስ ይላክለታል። «አርካዊው ኩሲ ልብሱን ቀድዶ በራሱም ላይ ትቢያ ነስንሶ ሊገናኘው መጣ። ዳዊትም አለው፦ ከእኔ ጋር ብትመጣ ትከብደኛለህ ወደ ከተማ ግን ተመልሰህ ለአቤሴሎም፡ - ንጉሥ ሆይ ባሪያ እሆንሃለሁ፤ አስቀድሞ ለአባትህ ባሪያ እንደ ነበርኩ እንዲሁ አሁን ለአንተ ባሪያ እሆንሃለሁ ብትለው የአኪጦፌልን ምክር ከንቱ ታደርግልኛለህ» (ቁ.33-34)። እግዚአብሔር ጸሎቱን ሰምቶ ወዲያውኑ የአኪጦፌልን ምክር ከንቱ የሚያደርግለትን ሰው ሲልክለት እናያለን።

## <u>ምዕራፍ አሥራ ስድስት</u>

ዳዊት ተሰዶ ከኢየሩሳሌም ከወጣ በኋላ የሜምፊቦስቴ ባሪያ ሲባ እንደተገናኘውና የሚያስፈልገውን ምግብና መጠጥ እንደሰጠው፤ እንዲሁም ሳሚ የሚባል የሳዖል ቤተሰብ የሆነ ሰው እየተራገመና ድንጋይ እየወረወረ ይከታተለው ነበረ። ያሳደደውም ልጁ አቤሴሎም ወደ ኢየሩሳሌም ከገባ በኋላ በአኪጦፌል ምክር አማካኝነት ወደ አባቱ ቁባቶች እንደገባና እግዚአብሔር በነቢዩ ናታን ምዕ. 12÷11 የተናገረው ከዓመታት በኋላ (አስራ ሁለት ዓመታት ያህል) እንደ ተፈጸመ እናነባለን።

ከዚህ ምዕራፍ አንዳንድ ነገሮችን እንማራለን

1. የሜምፊቦስቴ ባሪያ ለዳዊት በውሸት ሜምፊቦስቴን በማሳጣት «እነሆ የእስራኤል ቤት ዛሬ የአባቴን መንግሥት ይመልስልኛል ብሎ በኢየሩሳሌም ተቀምጧል» ብሎ ይነግረዋል። ዳዊትም ይህንን የማሳጣት ቃል ሰምቶ ሳይመረምር «እነሆ ለሜምፊቦስቴ የነበረው ሁሉ ለአንተ ይሁን።» በማለት ትክክለኛ ያልሆነ ፍርድን ያስተላልፋል። ምናልባት ዳዊት እንደዚህ ዐይነቱን ሚዛናዊ ያልሆነ ፍርድ እንዲያስተላልፍ ያደረገው በሜምፊቦስቴ ባሪያ በሲባ በኩል የመጣለት እጅ መንሻ ሳይሆን አይቀርም አንዳንድ ጊዜ ከስጦታና ከእጅ መንሻ ጀርባ ያለው መንፈስ ጤናማ ስላልሆነ እጅ መንሻውን ብቻ ሳይሆን ከጀርባው ያለውን መንፈስ መመርመር አለብን። ሲባ የተናገረው ነገር እውነት እንዳልሆነ የምናየው በምዕ. 19፥24 ላይ ነው። አቤሴሎም ከሞተ በኋላ ዳዊት ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሶ ንግሥናውን ከቀጠለ በኋላ፤ «የሳዖልም ልጅ ሜምፊቦስቴ ንጉሡን ሊቀበለው ወረደ፤ ንጉሡም ከሄደ ጀምሮ በደኅና እስከተመለሰበት ቀን ድረስ እግሩን አልጠገነም ጢሙንም አልቆረጠም፣ ልብሱንም አላጠበም ነበር። ንጉሡንም ሊቀበለው ከኢየሩሳሌም በመጣ ጊዜ ንጉሡ ሜምፊቦስቴ ሆይ፣ ከእኔ ጋር ስለምን አልወጣህም? አለው። እርሱም መልሶ አለ: - ጌታ ንጉሥ ሆይ፣ ባሪያዬ አታለለኝ፤ ... እርሱም እኔን ባሪያህን ለጌታዬ ለንጉሡ አማ።»

2. ሌላው ከምዕ. 16 የምንማረው ነገር በዳዊትና ዳዊትን ይራገም በነበረው ሰው መካከል ካለው ትዕይንት ነው። ሳሚ የሚባለው የሳዖል ዘር ዳዊትን እየተራገመና ድንጋይ እየወረወረ ይከተለዋል። ዳዊት ምንም ቢሰደድ አሁንም ንጉሥ ነው። ብዙ ሠራዊቶችም ተከትለውት ተሰድደዋል። አንዱን ተራ ወታደር ሄደህ ግደለው ቢለው ሊገድለው ይችል ነበር። ነገር ግን ዳዊት «ልሂድና ራሱን ልቁረጠው» ብሎ አንዱ የጦር አለቃ ሲናገር ሰምቶ ሲከለክለውና የሚያስገርም ነገር ሲመልስለት እናያለን። «እግዚአብሔር ዳዊትን ስደበው ብሎ አዝዞታልና ይርገመኝ ለምንስ እንዲህ ታደርጋለህ? የሚለው ማን ነው? አለ። ... እግዚአብሔር አዝዞታልና ተዉት ይርገመኝ። ምናልባት በዚህ ቀን መከራዬን አይቶ ስለ እርግማኑ መልካም ይመልስልኛል አላቸው።»

ከዚህ ክፍል የምንማረው፤ ዳዊት ይህ ሁሉ የደረሰበት በኦርዮን ላይ ስላደረገው ኀጢአት እንደሆነ ሳይገባው አይቀርም፤ ለእርሱ በውጭ ከሚካሄደው ውጊያና እርግማን ይልቅ <u>በውስጡ</u> እየተካሄደ ያለው ውጊያ ስላየለበት የውጪውን ውጊያ ብዙ ትኩረት አልሰጠውም። ለእርሱ ከሁሉ አስቀድሞ የታየው የእግዚአብሔርን ሞገስና ምሕረት ማግኘቱ ነው። «ምናልባት በዚህ ቀን መከራዬን አይቶ ስለ እርግማኑ መልካም ያደርግልኛል» ማለቱ፤ የውስጤን ውጊያ ድል አገኝ ዘንድ የውጪውን እታገሣለሁ ማለቱ ነው። የእግዚአብሔርን ሞገስ አገኝ ዘንድ የሰውን እርግማን እታገሣለሁ። ብዙ ጊዜ እንደ ክርስቲያኖች የምናደርገው የተገላቢጦሽ ነው። የውስጥ ውጊያ እያለብን ያንን ውጊያ ሳናሸንፍ የውጪ ውጊያ ላይ እናተኩራለን። በውስጣዊ ውጊያ እየተሸነፍን እስከ ሆነ ድረስ በውጬ ውጊያ ድል ብናገኝ ጠላትም ግድ የለውም። እንደውም ሐሳባችንን በውጬ ላይ ብቻ እንድናተኩር ስለሚፈልግ አውቆ የውጪን ውጊያ ድል ይተውልናል። የውስጣችን እየተቦረቦረ ከሄደ ቢዘገይም እንደምንወድቅ ያውቃል። ዳዊት ግን ከውጬ ይልቅ ያተኮረው የውስጡ ውጊያ ላይ ነበር። እግዚአብሔርም ያንን ተመልክቶ በመጨረሻ በውስጥም በውጭም ድል ይሰጠዋል።

1. በመጨረሻ የምንመለከተው ነጥብ፣ እግዚአብሔር በነቢዩ በናታን በኩል ከ 12 ዓመታት በፊት የተናገረው ትንቢት ሲፈጸም ነው።

ምዕ. 12፥11-12 «እግዚአብሔር እንዲህ ይላል: - እነሆ ከቤትህ ክፉ ነገር አስነሳብሃለሁ ሚስቶችህንም በዓይንህ ፊት እወስዳለሁ ለዘመድህም እሰጣቸዋለሁ፣ በዚህችም ፀሐይ

ፊት ከሚስቶችህ ጋር ይተኛል፡፡ አንተ ይህን በስውር አድርገሸዋል እኔ ግን ይህን በእስራኤል ሁሉ ፊትና በፀሐይ ፊት አደርገዋለሁ፡፡»

ይህ ቃል ከተነገረ በኋላ፤

ሀ. ዳዊት ከቤርሳቤህ ሰሎሞንን ወልዷል (ምዕ. 12÷24) - 1 ዓመት

ለ. አምኖን የአቤሴሎምን እህት ካስነወረ በኋላ፤ አቤሴሎም ሁለት ዓመት አድብቶ፣ አምኖን ይገደላል፡፡ (ምዕ 13 23) - 2 ዓመታት

ሐ. አምኖንን ከገደለ በኋላ ለሦስት ዓመታት ወደ ጌሹር ንጉሥ ሄዶ ተቀመጠ፡፡ (ምዕ. 13÷38) -3 ዓመታት

መ. ከዚያም በኢዮአብ አማካይነት ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሶ የንጉሥ ዳዊትን ፊት ሳያይ ለሁለት ዓመታት ተቀመጠ፡፡ (ምዕ. 14÷28) - 2 ዓመታት

ሠ. ከሁለት ዓመታት በኋላ ወደ ንጉሡ ገብቶ፣ ንጉሡም ተቀብሎ ስሞት ለአራት ዓመታት በቤተ መንግሥቱ በር አደባባይ እየቆመ ሴራ ሲጠነስስና የሕዝቡን ልብ ሲሠርቅ አሳለፈ፡፡ (ምዕ. 15÷1-7) - 4ዓመታት

በአጠቃላይ ናታን ለዳዊት «ከቤትህ ክፉ ነገር አስነሳብሃለሁ» ካለው በኋላ ያሉትን ዓመታት ብንደምር፤

1+2+3+2+4= በአጠቃላይ 12 ዓመታት እንዳለፉ እናያለን፡፡ ከዚህ ታሪክ የምንማረው እግዚአብሔር የተናገረው ነገር ምንም ቢቆይና ቢዘገይ መፈጸሙ እንደማይቀር ነው፡፡

## <u>ምዕራፍ አሥራ ሰባት</u>

አኪጦፌል በዳዊት ላይ ክፉ ምክር እንደመከረና ዳዊት በምዕ 15÷34 ላይ «የአኪጦፌልን ምክር ከንቱ አድርግልኝ» ብሎ በጸለየው መሠረት በኩሲ በኩል የአኪጦፌልን ምክር ከንቱ ያደርግለታል፡፡ የአኪጦፌል ምክር በዳዊት ላይ የተሰነዘረ ክፉ ምክር ቢሆንም ለአቤሴሎም ሐሳቡ እንዲቃና የሚረዳው ምክር ነበር፡፡ «እግዚአብሔር በአቤሴሎም ላይ ክፉ ያመጣ ዘንድ እግዚአብሔር መልካሚቱን የአኪጦፌልን ምክር እንዲበተን አዘዘ» (ቁ. 14)፡፡ የአኪጦፌል ምክር ምንም ክፉ ቢሆን ከምክሩ የምንማረው ነገር አለ፡፡ «አኪጦፌልም አቤሴሎምን፡- አሥራ ሁለት ሺህ ሰዎች ልምረጥና <u>በዚህች ሌሊት</u> ተነስቼ ዳዊትን ላሳድድ፡፡ ደክሞና እጁ ዝሎ ሳለ እወድቅበታለሁ አስፈራውማለሁ፣ ከእርሱም ጋር ያለው ሕዝብ ይሸሻል፣ ንጉሡንም ብቻውን እመታዋለሁ» ቁ. 1-2፡፡ የአኪጦፌል ምክር ለአቤሴሎም መልካም ለዳዊት ደግሞ አደገኛ የነበረበት ምክንያት የውጊያው ስልት ፋታ የማይሰጥ መሆኑ ነው፡፡ «በዚህ ሌሊት ተነሥቼ ዳዊትን ላሳድድ» የሚል ምክር ነበር፡፡ በእውነትም በዚያን ጊዜ ዳዊትና ሕዝቡ ደክመው ስለነበረ መዋጋትና መከላከል የሚችሉበት ጊዜ አልነበረም፡፡ ምዕ. 16÷14 ከአኪጦፌል ምክር የምንማረው፤ ጠላትን በምንዋጋበት ጊዜ ጠላት ሥር ሳይሰድ ከጅምሩ ጊዜ ሳናባክን መሆን እንዳለበት ነው፡፡ ጊዜ ከሰጠነው ተደራጅቶ ሥር ይሰድና በቀላሉ ልናሸንፈው እንችል የነበረው ጠላት ምሽግ መሸጎና የማይበገር ሆኖ ይጠብቀናል፡፡ ኩሲ የአኪጦፌልን ምክር ከንቱ ያደረገበት ጊዜውን በማራዘም ነበር፡፡ አኪጦፌል 12ሺህ ሰዎች ብቻ ይዤ በዚህ ሌሊት ልሂድ ነበረ ያለው፡፡ ኩሲ ግን ዳዊት የሚበረታታበትንና የሚዘጋጅበትን ጊዜ እንዲያገኝ ብሎ ጊዜው የሚራዘምበትን ሁኔታ ፈጠረ፡፡ ለሰልፍ የሚወጣውን ሕዝብ እንደ ባሕር አሸዋ አብዝተን፣ ከዳን እስከ ቤርሳቤህ እሥራኤል ሁሉ ይሰብስብና አንተ በመካከላቸው በሰልፍ ውጣ በማለት ይመክረዋል፡፡ ከዳን እስከ ቤርሳቤህ ከዳር እስከዳር ያለው ሕዝብ እስከሚሰበሰብ ብዙ ጊዜ

ስለሚፈጅ ዳዊትና ሕዝቡ በቂ ጊዜ ያገኛሉ ማለት ነው፡፡ በወቅቱ ቢሆን ኖሮ 12ሺህ ሰዎች ብቻ የሚያሸንፉት ውጊያ ጊዜው ካለፈ በኋላ እስራኤል ሁሉ ተሰብስቦ ቢዋጋ ሊያሸንፍ አልቻለም፡፡

በመጨረሻ ላይ አኪጦፌል ምክሩን እንዳልተቀበሉ ባየ ጊዜ ምክሬን ለምን አልተቀበሉም ብሎ በገዛ እጁ ታንቆ ሞተ፡፡  አንዳንድ ጊዜ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ በኅብረት ወይም በኮሚቴ በምንሠራበት ጊዜ የእኛ ሐሳብ ከሌሎች የተሻለ ሆኖ ሳለ ሌሎች ባይቀበሉን ለምን ሐሳቤ ተቀባይነት አላገኘም ብለን ሄደን ራሳችንን ባናንቅም ብዙ ነገሮችን ማበላሸት ይቻላል፡፡ በቀላሉ የመንፈስን አንድነት ማደፍረስና ማነቅ እንችላለን፡፡ ሌሎችን ማኩረፍ ወይም ስለ ሌሎቹ ቀና ያልሆነ ነገር ማሰብና መናገር እንጀምራለን፡፡ ቤተ ክርስቲያንን መረበሽና ማወክ እንጀምራለን፡፡ ይህ ሁሉ የሚያሳየው የአኪጦፌል መንፈስ በእኛ ላይ እንደሰፈረ ነው፡፡ በአንፃሩ ማድረግ ያለብን፤ መልካሚቱ ሐሳባችን ተቀባይነት ባታገኝም በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ነገር ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብር እንጂ ለእኛ ስምና ስሜት ስላልሆነ ለእግዚአብሔር ትተነው በትህትና የመንፈስን አንድነት ጠብቀን በእግዚአብሔር ቤት በእግዚአብሔር ፍርሃት መመላለስ አለብን፡፡ እግዚአብሔር ለክብሩ እንዲሆን ከወደደ ውድቅ የተደረገውን ሐሳባችንን እንደገና ሊያነሣው ይችላል፡፡ አለበለዚያ ግን ምናልባት እግዚአብሔር እኛን የሚመዝንበት ሁኔታ ሊሆን ስለሚችል ሲመዝነን ቀልለን እንዳንገኝ  እንጠንቀቅ፡፡

## <u>ምዕራፍ አሥራ ስምንት</u>

ይህ ምዕራፍ አቤሴሎምን አንግሠው የነበሩት የእስራኤል ሕዝብና የዳዊት ባሪያዎች እንደተዋጉና የእስራኤል ሕዝብ እንደተሸነፉ አቤሴሎምም እንደ ተገደለ የሚተርክ ምዕራፍ ነው፡፡

ከቁ. 1-5 ዳዊት ሠራዊቱን ሲያከፋፍልና ለሠራዊት አለቆቹ መመሪያ ይሰጣል፡፡ እርሱ ራሱም ከእነርሱ ጋር ወደ ጦርነት እንደሚወጣ ይነግራቸዋል፡፡ ሕዝቡ ግን አንተ ከእኛ ከአሥሩ ሺህ ትበልጣለህና ወደ ሠልፉ አትወጣም «በከተማ ተቀምጠህ ብትረዳን ይሻላል፡፡» በማለት ከጦርነት ያስቀሩታል፡፡ ይህ አባባል ጠቃሚ ሐሳብ አለበት፡፡ በእግዚአብሔር ቤትና በእግዚአብሔር ጦርነት ውስጥ የት ብንሆን እንደሚሻል ማወቅ አለብን፡፡ አንድ ጀኔራል እንደ አንድ ተራ ወታደር ከፊት ሄዶ ከሚዋጋ ይልቅ ከኋላ ሆኖ መመሪያና ድጋፍ መስጠቱ የበለጠ ለሠራዊቱ ጠቀሜታ ሊሆን ይችላል፡፡ ምክንያቱም እርሱ ከሞተ ምናልባት የእርሱን ቦታ የሚተካ ላይገኝ ይችላል፡፡

ዳዊት ለሠራዊቱ አለቆችና ለሕዝቡ ሁሉ ከሰጠው መመሪያዎች አንዱ፤ «ለብላቴናው ለአቤሴሎም ስለ እኔ ራሩለት» የሚል ነበረ፡፡ በመጨረሻም ጦርነቱ አልቆ የእሥራኤል ሕዝብ በዳዊት ባሪያዎች ከተሸነፉ በኋላ የዳዊት ጥያቄ «ብላቴናው አቤሴሎም ደህና ነውን?» የሚል ነበረ (ቁ. 29፣32)፡፡ ዳዊት፤ ያሳድደው ስለነበረው ልጁ የነበረውን የአባትነት ፍቅርና ርኅራኄ ስናይ የእግዚአብሔርን የአባትነት ፍቅርም በጥቂቱ ያሳየናል፡፡ አቤሴሎም፡ - አመጸኛ የሆነ፣ አባቱን ለማሳደድና ከዙፋን ለማውረድ ብቻ ሳይሆን ለመግደልም ወደ ኋላ የማይል ልጅ ነበረ በምዕ. 17÷1-2 አኪጦፌል ለአቤሴሎም አባቱን ዳዊትን ስለመምታት (ስለ መግደል) ሲያማክረው «ነገሩም አቤሴሎምንና የእስራኤልን ሽማግሌዎች ሁሉ ደስ አሰኘ» (ምዕ. 17÷4)፡፡ የሚል ቃል እናነባለን፡፡ በሙሴ ሕግም ቢሆን «እናቱንና አባቱን የሚሰድብ ፈጽሞ ይገደል፡፡» ስለሚል ሊገደል የሚገባው ልጅ ነበረ፡፡ ነገር ግን ዳዊት ለልጁ የነበረው ፍቅርና ርኅራኄ በጣም የሚያስገርም ነው፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ልጆቹ ያለውን ፍቅርና ርኅራኄ ያሳየናል፡፡ ምንም ስሙን በአሕዛብ ዘንድ የምናሰድብ ብንሆን፣ ምንም በኃጢአታችንና በአመጻችን ቁስሉን ደግመን ደጋግመን የምናቆስል ቢሆን፣ ምንም ንግሥናውን ከልባችን ዙፋን አውርደን በፋንታው ራሳችንን የምናነግሥ ቢሆን፣ ምንም ከሕይወታችን አውጥተን

የምናሳድደው ቢሆን፤ በደጃችን ቆሞ «እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ ማንም ድምፄን ቢሰማ፣ ደጁንም ቢከፍትልኝ ወደ እርሱ እገባለሁ፣ ከእርሱም ጋር እራት እበላለሁ፣ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል።» (ራእ. 3÷20) በማለት ደጅ ይጠናናል። ይህንን ቃል ጌታ የተናገረው ለማያውቁት ዓለማውያን ሳይሆን ለቤተክርስቲያን (ለአማኞች) እንደሆነ ማስተዋል አለብን። ከሕይወታቸውና ከልባቸው ዙፋን አሳድደውት ለነበሩ ክርስቲያኖች የተናገረው ቃል ነው።

ይህንን በሚመለከት፤ ከ2ሳሙ ምዕ. 18 የምናየው ሌላ ሐሳብ ደግሞ፤ ኢዮአብ የዳዊትን ለልጁ መንሰፍሰፍና መራራት እያወቀ አቤሴሎምን ከነነፍሱ መያዝ ሲችል እንደገደለው እናያለን። ይህ ምሕረት-አልባ የሆነ ድርጊት የሚያሳየን የብዙ ክርስቲያኖችንም ምሕረተ-ቢስነት ነው። ክርስቶስ የሚራራለትን፣ ምሕረቱን ሊያሳየው የሚፈልገውን ወንድም እኛ ብዙ ጊዜ ያለ ምሕረት ስንገድል እንገኛለን። በመጽሐፈ ኢዮብ ውስጥ ኢዮብ እንዲህ ይላል፤ «ሁሉን የሚችለውን የአምላክን መፍራት ለሚተው፣ ለመዛል ለቀረበው ስንኳ ወዳጁ ቸርነትን ሊያሳይ ይገባል» (ኢዮብ 6÷14)። በተጨማሪም ጳውሎስ በገላትያ 6÷1 እንዲህ ይላል፤ «ወንድሞች ሆይ፣ ሰው በማናቸውም በደል ስንኳ ቢገኝ፣ መንፈሳውያን የሆናችሁ እናንተ እንደዚህ ያለውን ሰው በየውሃት መንፈስ አቅኑት፤ አንተ ደግሞ እንዳትፈተን ራስህን ጠብቅ።»

ሌላው በዚህ ምዕራፍ የምናየው አሳዛኝ ነገር፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ እርስ በርሱ መጫረሱ ነው።

«የእስራኤል ሕዝብ በዳዊት ባሪያዎች ፊት ተመቱ፣ በዚያም ቀን ታላቅ ውጊያ ሆነ፣ ሃያ ሺህ ሰውም ሞተ» (ቁ. 7)። ብዙ ጊዜ የእስራኤል ሕዝብ ከውጭ ጠላቶች ጋር ሲዋጋ ይህንን ያህል ሕዝብ አያልቅም። እርስ በርሳቸው ሲዋጉ ግን የውጭ ጠላት ከሚያጠቃቸው የበለጠ አንዳቸው ሌላውን ሲያጠቁ እናያለን። በተጨማሪም፤ የአንድ ሰው (የአቤሴሎም) አመጽ ለዚህ ሁሉ እልቂት መንስዔ ሆነ።

በውጊያው ውስጥ አመጸኛ የነበሩት የአቤሴሎም ወገኖች ስለነበሩ እግዚአብሔር ተፈጥሮ እንኳን የዳዊትን ሠራዊት እንዲረዳ ሲያደርግ እናያለን። «በዚያም ቀን ሰይፍ ከዋጠው ሕዝብ ይልቅ <u>ዱር</u> ብዙ ዋጠ» (ቁ. 8) አቤሴሎምንም አንድ የዛፍ ቅርንጫፍ ውጦ አስቀረው። «አቤሴሎምም በበቅሎ ተቀምጦ ነበረ፣ በቅሎውም ብዙ ቅርንጫፍ ባለው በታላቅ ዛፍ በታች ገባ፣ ራሱም በዛፉ ተያዘ፣ በሰማይና በምድር መካከል ተንጠለጠለ፤ ተቀምጦበትም የነበረ በቅሎ አለፈ» (ቁ. 9)። ያስረዝም የነበረውና ውበት ብሎ ይመካበት የነበረው ጸጉር በቅርንጫፉ ስለተያዘ ማላቀቅ አልቻለም።

ከቁ. 19-30 የምናየው ስለ አንድ ሳይላክ ካልሮጥኩ የሚል ወሬኛ ሰው ነው። በንጉሡ ፊት መልካም ወሬን እያመጣ ምሥጋና መቀበል የለመደ ሰው ይመስላል። ኢዮአብ ይህንን ሰው ጥሩ ጥያቄ ይጠይቀዋል። «ልጄ ሆይ መልካምን ወሬ የምትወስድ አይደለህምና <u>ትሮጥ ዘንድ ለምን ትወዳለህ</u>?» (ቁ. 22) በእግዚአብሔር ቤት ሳንላክ ከመሮጥ እግዚአብሔር ይጠብቀን። «እርሱም፡ - እኔ ብሮጥ ምን ይገድዳል? አለ። እርሱም፡- ሩጥ አለው። አኪማአስም በሜዳው መንገድ በኩል ሮጦ ኩሲንም ቀደመው» (ቁ. 23)። እንደዚህ ዓይነት ሰዎች መሮጥና ማውራት ስለሚችሉ ብቻ ትክክለኛውን መልእክት ይዘው የተላኩትን እየቀደሙ እንቅፋት የሚሆኑ ናቸው። ይህ ሰው ንጉሡ ፊት ቀርቦም የያዘው መልእክት ንጉሡ ልብ አልደረሰም። «ንጉሡም ፈቀቅ ብለህ ቁም አለ፤ እርሱም ፈቀቅ ብሎ ቆመ።» (ቁ. 30)

## <u>ምዕራፍ አሥራ ዘጠኝ</u>

ይህ ምዕራፍ የዳዊትን ወደ አገሩ መመለስና በስደት ላይ በነበረበት ጊዜ ክፉም ደግም ያደረጉበትን ሰዎች አግኝቶ በምሕረትና በቸርነት እንዳስተናገዳቸው የሚናገር ክፍል ነው።

ከቁ. 1-8 ዳዊት ስለልጁ ስለ አቤሴሎም በጣም ስላዘነና ስላለቀሰ ሕዝቡ ከጦር ሜዳ ተሸማቆ እንደገባና ኢዮአብ ወደ ዳዊት ገብቶ እንደገሰጸው እናያለን። የኢዮአብ ተግሣጽ፤ መዳፈርና አመጽም (ማስፈራራት) እንደነበረበት እናያለን።

በቁ. 10 ላይ የእስራኤል ሕዝብ እንዲህ ይላሉ። «በላያችን እንዲሆን የቀባነው አቤሴሎም በሰልፍ ሞቶአል። አሁን እንግዲህ ንጉሡን ለመመለስ ስለምን ዝም ትላላችሁ።» ከዚህ ጥቅስ የምንማረው፣ አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔር ሕዝብ አመጸኛውንም ሰው የውጫዊውን ሁኔታ ብቻ አይተው ሊያነግሡ እንደሚችሉ ነው።

ከቁ. 15-23 የጌራ ልጅ ሳሚ፤ ዳዊት በኤቤሴሎም በተሰደደ ጊዜ እየተራገመ ይከታተለው የነበረው ሰው፣ በፊቱ ተደፍቶ «ኃጢአቴን አትቁጠርብኝ» በማለት ሲማጸነው፣ ዳዊትም ምሕረትን ከእግዚአብሔር የተቀበለ (መዝ. 51) ሰው ስለነበረ ይህንን ሰው ይቅር ሲለው እናነባለን። ዳዊት በመዝ. 51 «እኔ መተላለፌን አውቃለሁና» ብሎ ንስሐ ገብቶ እንደነበረ ሁሉ ሳሚም ዳዊትን «በደለኛ እንደሆንኩ አውቄአለሁና» ይለዋል። ዳዊትም «አትሞትም» ብሎ ይምልለታል። በአዲስ ኪዳንም የታዘዝነው ይህንኑ ነው። «እናንተ ግን ይቅር ባትሉ በሰማያት ያለው አባታችሁም ኃጢአታችሁን ይቅር አይላችሁም» (ማር. 11÷26)። የዳዊት ይቅርታ ግን ፍጹም እንዳልነበረ በ1ኛ ነገሥት 2÷8-9 እናያለን። እግዚአብሔር ይቅር ማለት ብቻ ሳይሆን ኃጢአታችንን ደግሞ እንደማያስብ የእግዚአብሔር ቃል ይነግረናል። ኢሳ. 43÷10 «መተላለፍህን ስለ እኔ ስል የምደመስስ እኔ ነኝ፤ ኃጢአትህንም አላስብም (አላስታውስም)»። ዳዊት ግን በ1ነገ. 2÷8-9 ልጁ ሰለሞንን ከነገሡ በኋላ የሳሚን ጉዳይ አስታውሶት «ሽበቱንም ከደም ጋር ወደ መቃብር አውርድ» ይለዋል። ምንም ስለማለለት ራሱ ባይገድለውም በእጅ አዙር ሲበቀለው እናያለን። ከቁ. 24-30 ያለውን የሜምፊቦስቴን ጉዳይ በምዕ. 16 ላይ አገናዝበን ስለተመለከትነው ደግመን አንመለከተውም። ከቁ. 31-39 ድረስ የሰማንያ ዓመት ሽማግሌ የነበረው ገለዓዳዊው ቤርዜሊ ዳዊት በስደት ላይ ሆኖ ይመግበው ስለነበረ አሁን ከስደት ሲመለስ ዳዊት ቸርነት ያደርግለታል። ዕድሜው የገፋ ስለነበረ ከዳዊት ጋር አብሮ ሄዶ ከንጉሥ ገበታ መቀለብን የሚያጓጓ ነገር አድርጎ ስላልተመለከተው አስገራሚ የሆነ መልስን በጥያቄ መልክ ለዳዊት ይመልስለታል። «<u>ከሕይወቴ ዘመን ምን ያህል ቀረኝ</u>?» በዚህች በቀረችኝ ጥቂት ዘመን ምግብና መጠጥ የማጣጥምበት (የማማርጥበት) ጊዜ አይደለም በማለት የንጉሡን ግብዣ ለዘመዱ ያስተላልፋል። «ንጉሡም ቤርዜሊን ሳመው፣ መረቀውም ወደ ስፍራውም ተመለሰ» (ቁ. 39)። ምርቃት ብቻ ሳይሆን ሰሎሞንን ካነገሡ በኋላ በ1ነገ 9. «ለቤርዜሊ ልጆች መልካም ቸርነት አድርግላቸው በማዕድህም ከሚበሉት መካከል ይሁኑ።» በማለት በረከቱን ለዘሩ ያስተላልፋል።

ከቁ. 40-43 የምናየው በእስራኤል ሕዝብና በይሁዳ ሕዝብ መካከል ስለተነሣው የቃላት ንትርክ ነው። ሁለቱም ወገኖች ሌላውን ዝቅ በማድረግ የራሳቸውን መብት ለማስጠበቅ ይሞክራሉ። ይህም ትሕትና የጎደለው ሁኔታ በሚቀጥለው ምዕራፍ ያለውን አመጽ ይወልዳል።

## ምዕራፍ ሃያ

በዚህ ምዕራፍ፤ ሳቤዔ የሚባል ብንያማዊ ሰው በዳዊት ላይ በማመጽ እንደተነሣና እስራኤልም ሁሉ (ከይሁዳ በስተቀር) እንደተከተለው እናያለን። በመጨረሻም የዳዊት ባሪያዎች አሳድደውት በአንዲት ብልሃተኛ ሴት አማካይነት ይገልጻል።

በዚህ ምዕራፍ መጀመሪያና መጨረሻ ላይ ሁለት መለከቶች ይነፋሉ። የመጀመሪያው በሳቤዔ የተነፋ የአመጽ መለከት ሲሆን በመጨረሻ ላይ ጦርነቱን ለማቆም ደግሞ በኢዮአብ የተነፋው የሰላም መለከት ነበረ። በእግዚአብሔር ቤትም ድምፅ ሲሰማ የሰላምም የአመጽም ሊሆን እንደሚችል ማስተዋል አለብን።

በምዕራፉ መካከል የምናየው ሌላ ትዕይንት፣ በአሜሳይና በኢዮአብ መካከል የተፈጸመው ሁኔታ ነው። አሜሳይ የአቤሴሎም የጦር አዛዥ ሆኖ ዳዊትን ለመውጋት ወጥቶ የነበረ ሰው ነው። በተጨማሪም፣ የኢዮአብ የአክስቱ ልጅ እንደሆነ በምዕ 17÷25 ላይ እናነባለን። ዘመዳሞች ቢሆኑም ሁለቱም የጦር አዛዦች ሆነው (አሜሳይ የአቤሴሎም፤ ኢዮአብ ደግሞ የዳዊት) እርስ በርስ ተዋግተው ነበረ። ጦርነቱ አልቆ ዳዊት ካሸነፈ በኋላ፣ ዳዊት በኢዮአብ ላይ ቅሬታ ስለ ነበረው (ቃሉን ተላልፎ ልጁን አቤሴሎምን ስለገደለበትና በምዕ. 19÷7 ላይ የማስፈራራትን ቃል ስለተናገረው) አሜሳይን በኢዮአብ ፈንታ የጦር አዛዥ ለማድረግ እንደሚፈልግ መልእክት ለአሜሳይ ይልክበታል ምዕ. 19÷13። ይህንን ወሬ ኢዮአብ ሳይሰማ ስለማይቀር በምዕ. 20 ላይ ወዳጅ መስሎ ቀረብ ይልና በሰይፍ አንጀቱን ወግቶ ይገድለዋል። በአገራችን «አፉ ቅቤ፣ ልቡ ጩቤ» የሚባለውን አባባል በግልጽ የምናየው በዚህ ክፍል ነው። «ኢዮአብም አሜሳይን፡ - ወንድሜ ሆይ ደኅና ነህን? አለው። ኢዮአብም አሜሳይን የሚስም መስሎ በቀኝ እጁ ጢሙን ያዘው። አሜሳይ ግን በኢዮአብ እጅ ከነበረው ሰይፍ አልተጠነቀቀም ነበር፣ ኢዮአብም ሆዱን ወጋው፣ አንጀቱንም በምድር ላይ ዘረገፈው፣ ሁለተኛም አልወጋውም፣ ሞተም።» (ቁ. 9-10)

ከዚህ ሁኔታ ቀጥሎ የምናየው፤ አንዲት ብልሃተኛ ሴት ሳቤዔ ተመሽጎበት የነበረው ከተማ በኢዮአብ ሠራዊት እንዳይፈርስና የብዙ ሰዎችም ሕይወት እንዳይጠፋ የፈጠረችውን መላ ነው። ሴት በተፈጥሮ ብዙ ጉልበት እንደሌላት እናውቃለን፤ ሆኖም የሌላትን ጉልበት ሳይሆን እግዚአብሔር የሰጣትን ብልሃት በመጠቀም ከኢዮአብ ጋር በመስማማት፣ ሳቤዔን የተከተሉትን ሕዝብም በብልሃትዋ በማሳመን፣ የሳቤዔን ራስ ቆርጠው ወደ ኢዮአብ እንዲጥሉለት አድርጋ ሊመጣ ከነበረው ታላቅ መፍረስና እልቂት ከተማዋን ታድናለች። ከዚህ የምንማረው፣ እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን የሰጠን ጸጋና ስጦታ የሚያስፈልግበት ጊዜ እንዳለ ነው። እኔ እንደ ኢዮአብ የጦር አዛዥ አይደለሁም፣ ኃይልና ጉልበት የለኝም ብለን ቁጭ ከምንል እግዚአብሔር የሰጠንን ማንኛውንም ጸጋና ስጦታ ለእግዚአብሔር ክብርና ለሰው ጥቅም ማዋል አለብን። «ሴቲቱም በብልሃትዋ ወደ ሕዝቡ ሁሉ ሄደች፣ እነርሱም የቢክሪን ልጅ የሳቤዔን ራስ ቆርጠው ወደ ኢዮአብ ጣሉት። እርሱም (ኢዮአብ) ቀንደ መለከቱን ነፋ፣ ሰውም ሁሉ ከከተማይቱ ርቆ እያንዳንዱ ወደ ድንኳኑ ሄደ» (ቁ. 22)። ከዚህ ታሪክ ሌላ የምንማረው ነገር፤ በቁ. 2 ላይ «የእስራኤል ሰዎች ሁሉ ከዳዊት ተለይተው የቢክሪን ልጅ ሳሌዔን ተከተሉ» ይላል። በቁ. 22 ላይ ደግሞ ይኸው ሳባዔን ተከትሎ የነበረ ሕዝብ፤ «የቢክሪን ልጅ የሳቤዔን ራስ ቆርጠው ወደ ኢዮአብ ጣሉት» የሚል ቃል እናነባለን። በአመጻችን ሕዝብ ሁሉ የተከተለን ቢመስለን እንኳን ያው የተከተለን ሕዝብ አሳልፎ እንደሚሰጠን እንወቅ። የአመጻ ዋጋ ሁልጊዜ በአመጽ መጥፋት ስለሆነ የተከተለን የሕዝብ ብዛት አያድነንም። ትልቁ ነገር እግዚአብሔር ከእኛ ጋር መሆኑ ነው። ስለዚህ ነው፣ ሙሴ «አንተ ከእኛ ጋር ካልወጣህ አንወጣም» ይል የነበረው።

## ምዕራፍ ሃያ አንድ

በዚህ ምዕራፍ የምናየው በዳዊት ዘመን ለሦስት ዓመታት ረሃብ እንደነበረና ዳዊት በዚያን ጊዜ ምን እንዳደረገ ነው።

ቁ. 1 «በዳዊትም ዘመን ሦስት ዓመት ያህል ቀጥሎ ረሃብ ሆነ፣ ዳዊትም የእግዚአብሔርን ፊት ጠየቀ።» ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው ዳዊት በመንግሥቱ ውስጥ ረሃብ ሲመጣ የጠየቀው እግዚአብሔርን ነበረ። እኛም በሕይወታችን ወይም እኛን በሚያገባን ነገር ሁሉ አንድ ነገር ሲመጣ መጠየቅ ያለብን እግዚአብሔርን ነው።

ቁ. 2 «እግዚአብሔርም የገባዖንን ሰዎች ስለ ገደለ በሳዖልና በቤቱ ላይ ደም አለበት አለ።» ይህ የእግዚአብሔር መልስ በጣም የሚያስገርምና ትምህርት አዘል መልስ ነው። የገባዖንን ሰዎች ታሪክ በመጀመሪያ የምናየው በኢያሱ ምዕራፍ 9 ነው። የገባዖን ሰዎች እግዚአብሔር ለእሥራኤላውያን የሰጠውን ድል ሰምተው ስለፈሩ በተንኮል ከሩቅ አገር እንደመጡ መንገደኞች መስለው ወደ ኢያሱ በመሄድ አታለውት እንዳይገድላቸው ቃል ኪዳን ያስገቡታል። ኢያሱ 9፥15 «ኢያሱም ከእነርሱ ጋር ሰላም አደረገ፣ በሕይወት እንዲተዋቸውም ከእነርሱ ጋር ቃል ኪዳን አደረገ፤ የማኅበሩም አለቆች ማሉላቸው።» ኢያሱ ቃል ኪዳን ከገባላቸው በኋላ ወደ 350 ዓመታት በተለያዩ መሳፍንት እስራኤል ስትተዳደር ቆይታ ሳዖል ይነግሣል። የእስራኤል ንጉሥ እንደመሆኑ መጠን በገባዖን ሰዎችና በኢያሱ መካከል የተደረገውን የቃል ኪዳን ልውውጥ ሳያውቅ ይቀራል ማለት ያስቸግራል። ነገር ግን ይህንን ቃል ኪዳን እያወቀ የገባዖንን ሰዎች እንደገደለ ነው የምንረዳው። ከዚህ ክፍል የምንማረው ትልቅ ትምህርት፣ እግዚአብሔር ምን ያህል ቃል ኪዳንን የሚያከብርና፣ የገባነውን ቃል ኪዳን ስናፈርስ ከእግዚአብሔር ዘንድ ቅጣት እንዳለ ነው። ኢያሱ ለገባዖን ሰዎች ቃል ኪዳን ከገባላቸው ጊዜ ጀምሮ እስከ ሳዖል ድረስ ከ350 ዓመታት በላይ፤ እንዲሁም ከሳዖል የገባዖንን ሰዎች ቃል ኪዳን ማፍረስ ጀምሮ እስከ የዳዊት ዘመን ረሃብ ድረስ በግምት ከ30-40 ዓመታት ያህል ቢሆንም እግዚአብሔር ዘመናትን ቆጥሮ የሳዖልን የቃል ኪዳን ማፍረስ ቅጣት ሲያመጣ እናያለን።

ዳዊት፣ ይህ ቅጣት በእርሱ ዘመን ሲመጣ፣ የእግዚአብሔር ሐሳብ በመጠየቅ ምክንያቱን ከተረዳ በኋላ የገባዖንን ሰዎች፤ «የእግዚአብሔርን ርስት ትባርኩ ዘንድ ምን ላድርግላችሁ? ማስተሰርያውስ ምንድነው?» ይላቸዋል (ቁ. 3)። የገባዖንም ሰዎች የእነርሱ ጉዳይ የብርና የወርቅ ካሳ ሳይሆን ከሳዖል ዘር ሰባት ሰዎች እንዲሰጣቸውና በእግዚአብሔር ፊት እንዲሰቅላቸው ይጠይቁታል። ዳዊትም ከዮናታን ልጅ ከሜምፊቦስቴ በስተቀር ከሳዖል ዘር የተወለዱ ሰባት ልጆችን አሳልፎ ለገባዖን ሰዎች ይሰጣቸዋል፣ እነርሱም በእግዚአብሔር ፊት ሰቀሏቸው። ይህ ሁኔታ፣ እንዴት በሳዖል ዓመጽ ልጆቹ ይሞታሉ? የሚል ጥያቄ በአእምሮአችን ሳይፈጥር አይቀርም። መቼም አንድ እርግጠኛ የሆነ ነገር አለ፤ እርሱም እግዚአብሔር በሥራው ሁሉ ጻድቅ እንደሆነ ነው። በዚህ ስፍራ ለምን ይህንን ሁኔታ እንደፈቀደ አናውቅም፤ ነገር ግን በሕዝቅኤል 18 ላይ ሁሉ በራሱ ኃጢአት እንጂ፣ ልጅ በአባቱ ኃጢአት እንደማይሞት በግልጽ እግዚአብሔር ተናግሯል። ስለዚህ፤ በዚህ ታሪክ በተከሰተው ሁኔታ እኛ ሙሉ ለሙሉ የማይገባን የእግዚአብሔር ቅን ፍርድ እንዳለበት ተረድተን ማለፍ ይኖርብናል እንጂ ልጆች በአባቶች ኃጢአት ይሞታሉ የሚለውን ሐሳብ የሚያስተላልፍ ታሪክ አይደለም።

የገባዖን ሰዎች የደም ዋጋ ከሳዖል ቤት ከተከፈለ በኋላ እግዚአብሔር የረሃቡን ዘመን እንዳቆመ እናያለን። «ከዚያም በኋላ እግዚአብሔር ስለ አገሩ የተለመነውን ሰማ» (ቁ. 14)። ይህ ቃል ትልቅ መልእክት አለው። አንዳንድ ጊዜ ጸሎትና ልመና ብቻ የማይሠራበት ጊዜ አለ። ከጸሎቱና ከልመናው ጋር መከናወን ያለበት ነገር ካለ እርሱን ሳናከናውን ዕድሜ ልካችንን ብንጸልይ የጸሎታችንን መልስ አናገኝም። ስለዚህ ነው ዮሐንስ መጥምቁ «የንስሐ ፍሬ አሳዩ» እያለ የንሥሐን ጥምቀት ሊጠመቁ ወደ እርሱ ይመጡ የነበሩትን ሰዎች ያሳስባቸው የነበረው። የአፍ ንሥሐ ብቻ እንደማይበቃ፣ ነገር ግን በተግባር መገለጽ እንዳለበት ሲያመለክታቸው ነው።

በዚህ ምዕራፍ ሁለተኛ ክፍል፣ እስራኤላውያን ከፍልስጥኤማውያን ጋር ሲዋጉ ዳዊት አብሮ ለጦርነት ሄዶ ነበር። በዚህ ውጊያ ላይ እያለ «ዳዊትም ደከመ» የሚል ቃል እናነባለን። ያ ትልቁን ጎልያድ የዘረረ፣ አንበሳንና ድብን በእግዚአብሔር መንፈስ ኃይል ይመታና ይገድል የነበረ፣ በእሥራኤልም ሆነ በፍልስጥኤም ስሙ የታወቀ ጀግና ሲደክም እናያለን። ኃይልና ብርታት ከእግዚአብሔር ነውና ማንም ጀግና ቢኖር የሚደክምበት ጊዜ አለ። «... ብላቴኖች ይደክማሉ፣ ይታክቱማል ጎበዛዝቱም ፈጽሞ ይወድቃሉ፤ እግዚአብሔርን በመተማመን የሚጠባበቁ ግን ኃይላቸውን ያድሳሉ » (ኢሳ. 40÷30-31)። ዳዊት በደከመ ጊዜ ከጦር አለቆች አንዱ የነበረው የጽሩያ ልጅ አቢሳ ከአንድ ፍልስጥኤማዊ ጦር ሲያድነው ፍልስጥኤማዊውንም ሲገድል እናያለን። በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ማናችንንም ብንሆን የወንድሞቻችን እርዳታ የሚያስፈልገን ጊዜ አለ። ዳዊት ከጥቂት ምዕራፎች በፊት አቢሳን፤ «እናንተ የጽሩያ ልጆች ሆይ እኔ ከእናንተ ጋር ምን አለኝ? ዛሬ ስለምን ጠላቶች ትሆኑኛላችሁ?» (2ሳሙ. 19÷22) በማለት ጠንከር ባለ ቃል ተናግሮት ነበር። አንዳንድ ጊዜ «ከእናንተ ጋር ምን አለኝ» ብለን የራቅናቸው ሰዎች በደከምንበት ጊዜ ከጠላት ጦር የሚድኑን ሊሆኑ ይችላሉ።

## ምዕራፍ ሃያ ሁለት

ይህ ምዕራፍ ዳዊት ከሳዖል እጅ ከዳነ በኋላ ለእግዚአብሔር የዘመረው መዝሙር ነው። ከጊዜ አንጻር ሲታይ ይህ ምዕራፍ በ1ኛ ሳሙኤል እንጂ በ2ኛ ሳሙኤል ውስጥ መሆን አልነበረበትም፤ ምክንያቱም ዳዊት ከሳዖል እጅ ሲድን የምናየው በ1ሳሙኤል ውስጥ ነው። ይህ የዳዊት መዝሙር በመዝሙረ ዳዊት 17 (18) ላይ ተደግሟል።

ይህንን የዳዊት መዝሙር በምናይበት ጊዜ ዳዊት ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን የግል ግንኙነትና እግዚአብሔር ለዳዊት ያደረገለትን ቸርነትና ጥበቃ ይናገራል።

ከቁ. 1-4 ዳዊት እግዚአብሔርን በግል የሚያውቅ ሰው እንደነበረ እናነባለን። በዚህ ክፍል ዳዊት ለእግዚአብሔር ዘጠኝ ያህል የቅጽል ስሞችን ይሰጠዋል።

- ዓለቴ፣ አምባዬ መድኃኒቴ
- ጠባቂዬ ጋሻዬና የረድኤቴ ቀንድ
- መጠጊያዬ፣ መሸሸጊያዬ
- በመጨረሻም «ምሥጋና የሚገባው» ይለዋል።

ከዚህ ክፍል የምንማረው እግዚአብሔርን በተለያዩ ገጽታዎች በግል ሕይወታችን ማወቅ እንዳለብን ነው። በአጠቃላይ፤ እግዚአብሔር በግል ሕይወታችን ቀውስ ሲመጣ «መድኃኒታችን» እንደሆነ፤ ጠላት ሊያጠቃን ሲመጣ እንዳንጠቃ የሚያደርገን «ዓለታችን፣ አምባችን፣ ጠባቂአችንና ጋሻችን» እንደሆነ ያሳየናል።

ከቁ. 5-6 የምናየው ሁኔታ ግን እንደዚህ በአምላኩ የሚደገፍና የሚታመን፣ አምላኩን የሚያውቅ ሰው እንዴት ይህ ይደርስበታል የሚያስብል ነው።

«የሞት ጣር ያዘኝ፤
የዓመፅ ፈሳሽም አስፈራኝ፤
የሲዖል ጣርም ከበበኝ፤
የሞት ወጥመድ ደረሰብኝ» ይላል።

ይህ ጥቅስ የሚያሳየን፤ ምንም እግዚአብሔርን ብናውቅና በእግዚአብሔር ብንታመንም መከራና ፈተና አይደርስብንም ማለት እንዳልሆነ ነው። «በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ» ብሎ

አስጠንቅቆናል። በእግዚአብሔር መታመናችንና እግዚአብሔርን ማወቃችን የሚፈተነው በመከራና በፈተና ውስጥ በምናደርጋቸው ነገሮች ነው። በመከራና በፈተና ውስጥ በእግዚአብሔር የምናጉረመርም፣ በእግዚአብሔር የምናማርር፣ እግዚአብሔርን የምንረሳ ከሆነ ከጅምሩም እግዚአብሔርን እንደሚገባ አላወቅነውም ማለት ነው።

ዳዊት በሞት ጣር ውስጥ ሲያልፍ ምን እንዳደረገ በቁ. 7 ላይ እናነባለን።

«በጨነቀኝ ጊዜ እግዚአብሔርን ጠራሁት
ወደ አምላኬም ጮኽሁ
ከመቅደሱም ቃሌን ሰማኝ
ጩኸቴም በፊቱ ወደ ጆሮው ገባ።»

ከአምላኩ ሌላ መሄጃ ስላልነበረው ወደ አምላኩ ሲጮህ እናያለን። ጴጥሮስም ጌታን «ከአንተ ወዴት እንሄዳለን» ብሎ ነበር የመለሰለት።

ከቁ. 8-20 እግዚአብሔር ለዳዊት ጩኸት የሰጠውን መልስ እናያለን።

«ምድር ተንቀጠቀጠች፣ ተናወጠችም፣ የሰማዮችም መሠረቶች ተነቃነቁ፤
እግዚአብሔር ተቆጥቷልና ተንቀጠቀጡ።
ልዑልም ቃሉን ሰጠ
ፍላጻውን ላከ፣ በተናቸውም
መብረቆችን ላከ፣ አወካቸውም።
ከላይ ሰደደ፣ ወሰደኝም
ከብዙ ውሆችም አወጣኝ
ከብርቱዎች ጠላቶቼ
ከሚጠሉኝም አዳነኝ፤ በርትተውብኝ ነበርና።...»
ከዚህ ክፍል የምናየው፤ እግዚአብሔር ለባርያዎቹ ጩኸት የሚሰጠው መልስ፣ ምድርንና ሰማይን እስከማናወጥ እንደሆነ ነው። «ምድር ተንቀጠቀች ተናወጠችም፤ የሰማዮችም መሠረቶች ተነቃነቁ።»

ከቁ. 21-37 ዳዊት እንደገና ስለ እግዚአብሔር ባሕርይና ከእግዚአብሔር ጋር ስላለው ግንኙነት ይቀኛል።

ከዚህ ክፍል አንድ ጠጋ ብለን የምንመለከተው ቃል አለ፤

«... ተግሣጽህም አሳደገኝ።
አረማመዴን በበታቼ አሰፋህ፣
እግሮቼም አልተንሸራተቱም» ይላል። (ቁ. 36-37)

የእግዚአብሔር ተግሣጽ ለእድገታችን በጣም አስፈላጊ እንደሆነ ነው የምናየው። በምሳሌ ውስጥ «ተግሣጽን የሚጠላ ነፍሱን ይጠላል» ይላል። የእግዚአብሔርን ተግሣጽ በምንቀበልበት ጊዜ በሕይወታችን እናድጋለን፤ በሕይወት ጎዳና ተደላድለን መጓዝ እንችላለን።

ከቁ. 38-51 እግዚአብሔር በጠላቶቹ ሁሉ ላይ ድልን እንደሠጠው፣ አሕዛብን ከበታቹ እንደሚያስገዛለትና ድል በድል እንዳደረገው በመናገር ይቀኛል።

የዚህን ምዕራፍ ይዘት በቅድም ተከተል ብንመለከት፤

1. ከሁሉ በፊት እግዚአብሔር  አምላካችንን ማወቅ አለብን።
2. እግዚአብሔርን ብናውቅም መከራ አይደርስብንም ማለት አይደለም። የሞት ጣር እስኪ.ይዘን ድረስ ልንፈተን እንችላለን።
3. በመከራ ውስጥ እያለን ወደ አምላካችን መጮኽ አለብን።
4. እግዚአብሔር ለጩኸታችን መልስ በመስጠት ይታደገናል።
5. በዚህም ምክንያት እግዚአብሔርን የበለጠ ለማወቅና የበለጠ ወደ እርሱ ለመጠጋት እንችላለን።
6. በመከራ ተፈትነን ከወጣን በኋላ እግዚአብሔር ድል በድል ያደርገናል፣ ይሾመናል።

«የአሕዛብ ራስ አድርገህ ትሾመኛለህ የማላውቀው ሕዝብም ይገዛልኛል (ቁ. 44)።

## ምዕራፍ ሃያ ሦስት

ይህ ምዕራፍ የዳዊትን የመጨረሻ ቃልና የዳዊትን ኃያላን ጀብዱ ይዘረዝራል።
በቁ. 1 ላይ ስለ ዳዊት ማንነት ሲገልጽ ሁለት ነገሮችን ይናገራል።

1. «ከፍ ከፍ የተደረገው»
2. «በያዕቆብም አምላክ የተቀባው»

እነዚህ ሁለት ገለጻዎች ለማንኛውም የእግዚአብሔር ሰው አስፈላጊ ቅድመ ነገሮች ናቸው። ሰው ራሱን ከፍ ከፍ ማድረግ ይችላል፤ ውጤቱም ውድቀት ነው። እግዚአብሔር ከአፈር ላይ አንሥቶ ከፍ ከፍ የሚያደርገውን ሰው ግን ምንም ነገር አይጥለውም። ስለዳዊት የተነገረው ሁለተኛው ነገር በያዕቆብ አምላክ <u>መቀባቱ</u> ነው። በእግዚአብሔር ካልተቀባን በስተቀር ለእግዚአብሔርም ሆነ ለሰው የሚረባ ነገር ማድረግ አንችልም። መልካምን ነገር ሁሉ እንድናከናውን የሚረዳን የእርሱ ቅባት ነው። «ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም» (ዮሐ. 15፥5) ብሏልና። በእግዚአብሔር ከፍ ከፍ የመደረጉና የመቀባቱ ውጤት «መልካም ባለ ቅኔ» እንዳደረገው በዚሁ ቁጥር ላይ ይገልጻል።

በቁ. 2 ላይ ዳዊት ነቢይም እንደነበረ የሚገልጽ ቃል እናያለን። «የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ተናገረ ቃሉም በአንደበቴ ላይ ነበር» ይላል።

በቁ. 3 እና 4 ላይ እግዚአብሐር ለዳዊት፣ በሰዎች ላይ በጽድቅ ስለመሠልጠንና ስለ መንገሥ የተናገረውን ይዘረዝራል።

«በሰው ላይ በጽድቅ የሚሠለጥን፣
በእግዚአብሔር ፍርሃት የሚነግሥ፣
እርሱ እንደማለዳ ብርሃን እንደ ፀሐይ አወጣጥ
በጥዋትም ያለ ደመና እንደሚደምቅ

ከዝናብ በኋላ ከምድር እንደሚበቅል ልምላሜ ይሆናል።»

ይህ ክፍል፤ ትክክለኛ ባለሥልጣን ምን ዓይነት ሰው መሆን እንዳለበት ያስረዳል። በአገርም ላይ ቢሆን፣ በኅብረተሰብ ወይም በቤተሰብ ወይም በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ማንኛውም ሥልጣን በጽድቅና እግዚአብሔርን በመፍራት መሆን እንዳለበት ያመለክታል። እንደዚህ ዓይነት ባለሥልጣን ደግሞ እንደ ማለዳ ብርሃን አምሮ እንደሚወጣና እንደሚደምቅ ይናገራል። አለበለዚያ፣ መሰልጠን ሳይሆን መሰይጠን ይሆናል።

በቁ. 5 ላይ እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር ስለገባው ቃል ኪዳን ይናገራል። «ከእኔም ጋር በሁሉ ነገር ቅንና ጽኑ የሆነውን የዘላለም ቃል ኪዳን አድርጓል መድኃኒቴንና ፈቃዴን ሁሉ ያበቅላል።»

የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን፤

1. ቅን፡ - ምንም ክፉ ሐሳብ የሌለበት፤ «ለእናንተ የማስባትን ሐሳብ እኔ አውቃለሁ ፍጻሜና ተስፋ እሰጣችሁ ዘንድ የመልካም ሐሳብ እንጂ የክፉ አይደለም።» ኤር. 29÷11

2. ጽኑ ማንም የማያነቃንቀው፣ ማንም የማያፈርሰው ዋስትና ያለው፤ «ሁሉን ታደርግ ዘንድ ቻይ እንደሆን፣ አሳብህም (ቃል ኪዳንህም) ይከለከል ዘንድ ከቶ እንደማይቻል አወቅሁ።» ኢዮብ 42÷2

3. ዘላለማዊ፡ - ዘመን የማይሽረው እንደሆነ ይገልጻል።

በዚህም ቃል ኪዳን ውስጥ መድኃኒትንና በጎ ፈቃዳችንን እንደምናገኝ ያስረዳል።
«... ኃጢአትሽን ሁሉ ይቅር የሚል ደዌሽንም ሁሉ የሚፈውስ ምኞትሽን (ፈቃድሽን) ከበረከቱ የሚያጠግባት» መዝ. (103) 3-5

በዚህ ምዕራፍ ሌላ የምናየው የዳዊትን ኃያላን ስምና ያደረጉትን ጀብዱ ነው (ከቁ. 8-39)።

ከእነዚህ ጀግኖች ውስጥ አንዳንዶቹን ቀረብ ብለን እንመለከታለን።

ከቁ. 9-10 ኤልያናን የሚባለው ጀግና ያደረገውን ይገልጻል። «... ፍልስጥኤማውያንን በተገዳደሩ ጊዜ ከዳዊት ጋር ከሦስት ኃያላን አንዱ እርሱ ነበር፤ የእስራኤልም ሰዎች ተመለሱ። እርሱ ግን ተነሥቶ እጁ እስኪደክምና ከሰይፉ ጋር እስኪጣበቅ ድረስ ፍልስጥኤማውያንን መታ፤ በዚያም ቀን እግዚአብሔር ታላቅ መድኃኒት አደረገ፤ ሕዝቡም ከእርሱ በኋላ ምርኮ ለመግፈፍ ብቻ ተመለሰ።» ይህ ጀግና ሌሎቹ ሁሉ ጠላቶቻቸውን ለማጥቃት ከወጡ በኋላ ፈርተው ሲመለሱ እርሱ ግን ብቻውን (ከእግዚአብሔር ጋር) ጠላቶቹን ሲያጠፉ እናያለን። ይህ ታሪክ የሚያስተምረን ከብዙኃኑ ጋር አብረን ከሰልፍ መመለስ እንደሌለብን፤ ነገር ግን ከእግዚአብሔር ጋር በመቆም በእግዚአብሔር ኃይል ጠላታችንን መዋጋት እንዳለብን ነው። ዮናታን፤ «በብዙም ሆነ በጥቂት ማዳን አይሳነውም።» እንዳለ፤ ከአንድ ሰው ጋርም ብቻ ቢሆን እግዚአብሔር ይቆማል።

የሚቀጥለው ጀግና ደግሞ በቁ. 11-12 ተጠቅሷል። ስሙ ሣማ ይባላል። ይህ ሰው፤ እስራኤል ሁሉ ከፍልስጥኤማውያን ፊት ሲሸሹ፤ «እርሱ ግን በእርሻው መካከል ቆሞ ጠበቀ፣ ፍልስጥኤማውያንንም ገደለ፤ እግዚአብሔርም ታላቅ መድኃኒት አደረገ።» አጠገባችን ያለው ሕዝብ ሁሉ ቢሸሽ በእግዚአብሔር ታምነን፣ ጸንተን መቆም እንዳለብን ያስተምረናል።

«በክፉው ቀን ለመቃወም፣ ሁሉንም ፈጽማችሁ ለመቆም እንድትችሉ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ አንሱ» (ኤፌ. 6፥13)። የሚገባውን የጦር ልብስ ካልለበስን ክፉው በሚቃወመን ጊዜ ጸንተን መቆም እንደማንችል ያስረዳል።

ከዚህ ሰው ታሪክ ቀጥሎ የሦስቱ ኃያላን ታሪክ ተጽፎአል። (ከቁ. 13-17)

እነዚህ ሦስት ኃያላን፣ ዳዊት ከቤተልሔም ምንጭ ማን ባጠጣኝ? ብሎ በሚመኝበት ጊዜ የንጉሣቸውን ምኞት ለማርካት ብለው በፍልስጥኤማውያን ተይዛ ወደነበረችው ቤተልሔም ከተማ የጠላትን ሠራዊት በመቅደድ ሄደው ከምንጩ ውኃ ይዘውለት እንደመጡ እናነባለን። ከዚህ ክፍል የምንማራቸው ሁለት ነገሮች አሉ።

1. ብዙ ጊዜ የእግዚአብሔር ዓላማና ዕቅድ ባለባቸው ቦታዎችና ሰዎች ላይ የእግዚአብሔር ዓላማና ዕቅድ እንዳይፈጽም ጠላት ያንን ቦታ ወይም ያንን ሰው መቆጣጠር ይፈልጋል።

   «የፍልስጥኤማውያን ጭፍራ በዚያ ጊዜ በቤተልሔም ነበረ።» እግዚአብሔር ከቤተልሔም ሕዝቡን የሚያረካ ምንጭ እንዳዘጋጀ ጠላት ስለሚያውቅ ያችን ከተማ በቁጥጥሩ ሥር አድርጎ ነበር። ለወደፊትም የሕይወት ውኃ ምንጭ የሆነው መሲህና አዳኝ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሚመጣባት ከተማ ነበረች።

2. «ከዚህ ክፍል ሌላ የምንማረው ነገር፤ እነዚህ ሦስት ኃያላን የእግዚአብሔርን ሐሳብና ፈቃድ ይዘው፣ በመንገዳቸው ላይ የጠላት መጋረጥ ሳይበግራቸው የጠላትን ሠራዊት ቀድደው የንጉሣቸውን ምኞት ከግብ አደረሱ። አንድ ነገር የእግዚአብሔር ፈቃድና ሐሳብ መሆኑን ካወቅን ምንም ዓይነት ነገር በመንገዳችን ቢጋረጥ ሊበግረን እንደማይገባ ያስተምረናል። በእኛ ውስጥ ያለው በዓለም ካለው ስለሚበልጥና «... በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣንን ሰጥቻችኋለሁ » (ሉቃ. 10፥19)። ብሎ ጌታ ቃል ስለገባልን የእግዚአብሔርን ሐሳብ ከግብ እንዳናደርስ ምንም ነገር ምክንያት ሊሆን አይችልም።

   ከ2ሳሙ. 23፥25-39 ከተዘረዘሩት የዳዊት ኃያላን ውስጥ፣ የጊሎናዊው የአኪጦፌል ልጅ ኤልያብና ኬጢያዊው ኦርዮ ይገኙባቸዋል። እነዚህ ሁለት ስሞች ካለፍናቸው ታሪኮች ጋር የተያያዙ ስሞች ናቸው። ጊሎናዊው አኪጦፌል፣ አቤሴሎምን ተከትለው በዳዊት ላይ ካመጹት ሰዎች በምክር ዋነኛ የነበረው፣ በኋላም ምክሬን ለምን አልሰሙኝም ብሎ ራሱን የገደለው ነው። ነገር ግን ልጁ ኤልያብ ለዳዊት ታማኝ ሆኖ እንደውም ከዳዊት ኃያላን መካከል አንዱ መሆኑ ያስገርማል። አባት፣ ዳዊትን ሄጄ ካልገደልኩ የሚል ልጅ ግን ከዳዊት ጀግኖችና ጠባቂዎች አንዱ ነበር። በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ጤናማ ያልሆነ መከፋፈል በሚኖርበት ጊዜ ይህንን ዓይነት ችግር ነው የሚያመጣው። ልጅን ከአባት፣ ባልን ከሚስት ወንድምን ከወንድም እስከመለያየት ይደርሳል። ሌላው በዝርዝር ውስጥ የምናየው ሰው ኬጢያዊው ኦርዮ ነው። ይህ ጀግና ደግሞ ዳዊት ከቤርሳቤህ ጋር በዝሙት በወደቀ ጊዜ ያስገደለው የቤርሳቤህ ባል የነበረው ኦርዮ ነው። ይህንን ታሪክ ስናጠና እንደጠቀስነው ዳዊት ያስገደለው አሉኝ ከሚላቸው ጀግኖች አንዱን ነበር።

## በምዕራፍ ሃያ አራት

ላይ ዳዊት ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ እስራኤልን ለመቁጠር እንደተነሳሳና በእስራኤል ሕዝብ ላይ መቅሠፍት እንደመጣ፣ እንዲሁም መቅሠፍቱ እንዲከለከል ዳዊት መሥዋዕትን እንዳቀረበ እናያለን።

ይህ ምዕራፍና 2ዜና 21 ያንኑ ታሪክ የሚተርኩ ምዕራፎች ስለሆኑ አብረው ቢነበቡ መልካም ነው። 2ሳሙ. 24÷1 «ደግሞም የእግዚአብሔር ቁጣ በእስራኤል ላይ ነደደ፣ ዳዊትንም ሂድ እስራኤልንና ይሁዳን ቁጠር ብሎ በላያቸው አስነሳው።» ይላል።

1ኛ ዜና 21÷1 ደግሞ «ሰይጣንም በእስራኤል ላይ ተነሣ እስራኤልንም ይቆጥር ዘንድ ዳዊትን አንቀሳቀሰው።» ይላል። ሁለቱን በአንድነት ስናይ በ2ኛሳሙ. 24÷1 ላይ እግዚአብሔር ዳዊትን አነሳሳው ማለቱ ሳይሆን ሰይጣን እንዲያነሳሳው እንደፈቀደ ነው የምናየው። በእነዚህ በሁለት ምዕራፎች የምናየው ሌላ ነጥብ የሕዝቡ ቁጥር ብዛት ነው። በ2ኛ ሳሙ 24÷9 ላይ «ኢዮአብም የሕዝቡን ቁጥር ድምር ለንጉሡ ሰጠ «በእስራኤልም ሰይፍ የሚመዝዙ ስምንት መቶ ሺህ ጽኑዓን ሰዎች ነበሩ የይሁዳም ሰዎች አምስት መቶ ሺህ ነበሩ።» ይላል። በ1ዜና 21÷5 ላይ ደግሞ፤ «ኢዮአብም የቆጠራቸውን የሕዝብ ድምር ለዳዊት ሰጠ ከእስራኤልም ሁሉ አንድ ሚሊዮን ከመቶ ሺህ ሰይፍ የሚመዝዙ ሰዎችን አገኘ ከይሁዳም አራት መቶ ሰባ ሺህ ሰይፍ የሚመዝዙ ሰዎችን አገኘ።» ይላል። በእነዚህ ሁለት ክፍሎች ስላለው የቁጥር ልዩነት የተለያዩ ሐሳቦች ቢኖሩም ጥሩ ገለጻ ነው ተብሎ የሚታመነው፤ በእስራኤል ውስጥ ስለተገኙት ሰይፍ የሚመዝዙ ሰዎች ቁጥር  በ2ሳሙ. 24 -800,000 በ1ዜና 21 ደግሞ 1ሚሊዮን 1መቶ ሺህ ልዩነቱ 300,000 የሆነበት ምክንያት በ1ዜና 27÷1-15 ስናነብ በየወሩ ንጉሡን የሚያገለግሉና የሚጠብቁ በተጠንቀቅ ያሉ ሠራዊቶች እንደነበሩ ይናገራል። እነዚህ ሠራዊቶች ለ12ቱ ወራት የሚፈራረቁ በየወሩ 24,000 ብዛት ያላቸው፤ በአጠቃላይ 12×24,000=288,000 ያህል የሆኑ ሠራዊቶች ነበሩ። በተጨማሪም ንጉሡንና መኳንንቱን የሚያገለግሉ ከየነገዱ የሺህ አለቆች እንደነበሩ በ1ዜና 27÷1 እና 28÷1 እናነባለን ምናልባት እነዚህ ከየነገዱ የነበሩት ሺህ አለቆች ሥር የነበሩ ሌሎች 12,000 የቅርብ የንጉሡ አገልጋዮች ሳይሆኑ አይቀሩም። እነዚህን 12,000 ሠራዊቶች ከ288, 000 ሠራዊቶቹ ጋር ስንደምር 300,000 ይሆናሉ። እነዚህ ሠራዊቶች በኢዮአብ ከተቆጠሩት ውስጥ በንጉሡ ዳዊት መዝገብ እንዳልተጻፉ በ1ዜና 27÷24 ላይ እናነባለን። «የጽሩያ ልጅ ኢዮአብ መቁጠር ጀመረ፣ ነገር ግን አልፈጸመም ስለዚህም በእስራኤል ላይ ቁጣ ሆነ፣ ቁጥራቸውም በንጉሡ በዳዊት መዝገብ አልተጻፈም።» ይላል። ከዚህ የምንረዳው የእነዚህ ሠራዊቶች ቁጥር በ2ሳሙ 24 ላይ ባለው መዝገብ ውስጥ እንዳልገባ ነው። ይህንን ሐሳብ የሚደግፍ የቃላት ልዩነት በ2ሳሙ 24÷9 ላይ ... «በእስራኤልም ሰይፍ የሚመዝዙ ስምንት መቶ ሺህ ጽኑአን ሰዎች ነበሩ...» ሲል በ1ዜና 21÷5 ግን «... ከእስራኤልም ሁሉ አንድ ሚሊዮን ከመቶ ሺህ ሰይፍ የሚመዝዙ ሰዎችን አገኘ...» ይላል። የቃላቱ ልዩነት፤ «በእስራኤልም» በሚለውና «ከእስራኤልም» ሁሉ በሚለው መካከል ነው። አንደኛው የበለጠ ያካተተው ቁጥር እንዳለ ያመለክታል። በእንግሊዝኛው፤ "In Israel" እና " All Israel" የሚል ልዩነት አለ።

በይሁዳ ሠራዊት መካከል ስላለው የ30,000 ሠራዊት ቁጥር ልዩነት፣ ማለትም በ2ሳሙ. 24 ላይ 500,000 ሲል በ1ዜና 21 ላይ 470,000 ማለቱ ምናልባት በ2ሳሙ. ቁጥሩን ወደሚቀርበው መቶሺህ /Round Figures/ ወስዶት ይሆናል ወይም አንዳንዶች እንደሚሉት በ2ሳሙ. 6÷1 ያሉት የዳዊት ምርጥ የሆኑ 30,000 ሰዎች ከእስራኤል የተመረጡ ቢላቸውም ከይሁዳ ከራሱ ወገን ሳይሆኑ አይቀሩም። ምናልባት እነዚህ 30,000 ሠራዊቶች ሳይቆጠሩ ቀርተው ይሆናል። ዋናው ነገር ይህ የሕዝብ ቆጠራ በእግዚአብሔር መልካም ፈቃድ እንደተደረጉት የሕዝብ ቆጠራዎች ሳይሆን እንደውም እግዚአብሔር የተቆጣበትና ሕዝቡን የቀሰፈበት፣ የሠራዊቱ አለቃም ኢዮአብ ያልተቀበለውና ያላመነበት በሰይጣን አነሳሽነት የተደረገ ስለሆነ እንደዚህ ዓይነት የቁጥር መዛባት መኖሩ አያስደንቅም። ቆጣሪው ራሱ ያላመነበትና በአግባቡ ያልተመዘገበ የሕዝብ ቆጠራ ነበር። በአንደኛው መዝገብ የገባው በሌላው አልገባም ነበር ማለት ነው።

ሕዝቡን ከቆጠረ በኋላ የእግዚአብሔር ቅጣት በዳዊትና በሕዝቡ ላይ እንደመጣ እናያለን፡፡

«ሕዝቡንም ከቆጠረ በኋላ ዳዊትን ልቡ መታው፤ ዳዊትም እግዚአብሔርን ባረግሁት ነገር እጅግ በድያለሁ፤ አሁን ግን፣ አቤቱ ታላቅ ስንፍና አድርጌአለሁና የባርያህን ኃጢአት ታርቅ ዘንድ እለምንሃለሁ አለው፡፡» ይህንን ታሪክ ስናነብ የዳዊት ሕዝቡን መቁጠር በእግዚአብሔር ፊት ለምን በደል ሆነበት የሚል ጥያቄ በአእምሮአችን ይፈጠራል፡፡ በደል የሆነበት አንድ ሁለት ብሎ ሕዝቡን ማስቆጠሩ ሳይሆን ሕዝቡን ያስቆጠረበት የልቡ ግፊት (Motive) መሆን አለበት፡፡ ምክንያቱም ከዚህ በፊት የእስራኤል ሕዝብ ቆጠራ ያለምንም መቅሠፍት ሲካሄድ በዘኁልቁ መጽሐፍ አይተናል፡፡ ዳዊት ኢዮአብንና የሠራዊት አለቆችን ሕዝቡን እንዲቆጥሩ ሲያዛቸው ኢዮአብ የዳዊት ትእዛዝ ጤናማ እንዳልነበረ ያስተዋለ ይመስላል፡፡ «ኢዮአብም ንጉሡን፡ - የጌታዬ የንጉሡ ዓይን እያየ አምላክህ እግዚአብሔር ዛሬ ካለው ሕዝብ መጠን በላይ መቶ እጥፍ ይጨምርበት፤ ጌታዬ ንጉሡ ይህን ነገር ለምን ይወዳል፤ አለው» (2ሳሙ. 24÷3)፡፡ በ1ዜና 21÷3 ላይ «... በእስራኤል ላይ በደል ስለምን ይመጣል?» የሚል ቃል ይጨምርበታል፡፡ በአጠቃላይ ክፍሉን ስናይ የዳዊት በደል፤ ከእግዚአብሔር ይልቅ በሠራዊቱ ብዛት ወደመታመን ልቡ ስላዘነበለ ይመስላል፡፡ ዳዊት በተለያዩ ጊዜያት፤

«ንጉሥ በሠራዊቱ ብዛት አያመልጥም

«ፈረስም ከንቱ ነው አያድንም

በኃይሉም ብዛት አያመልጥም

እነሆ የእግዚአብሔር ዓይኖች ወደሚፈሩት ናቸው

በምሕረቱም ወደሚታመኑ» (መዝ. 33÷16-18)

እንዲሁም፤

«እነዚያ በሠረገላ እነዚያም በፈረስ ይታመናሉ፤ እኛ ግን በአምላካችን በእግዚአብሔር ስም ከፍ ከፍ እንላለን፡፡ እነርሱ ተሰነካክለው ወደቁ፤ እኛ ግን ተነሣን ጸንተንም ቆምን፡፡» መዝ. 20÷7-8 በማለት የሚተማመነው በአምላኩ እንጂ በሠራዊቱ ብዛት እንዳልሆነ ተቀኝቷል፡፡

በወጣትነቱም ዘመን ጎልያድን ሊወጋ ሲሄድ «... አንተ ሰይፍና ጦር ጭሬም ይዘህ ትመጣብኛለህ፤ እኔ ግን በተገዳደርከው በእስራኤል ጭፍሮች አምላክ ስም በሠራዊት ጌታ በእግዚአብሔር ስም እመጣብሃለሁ፡፡ እግዚአብሔርም ዛሬ አንተን በእጄ አሳልፎ ይሰጣል፡፡ ... ይኸውም ምድር ሁሉ እግዚአብሔር በሰይፍና በጦር የሚያድን እንዳይደለ ያውቅ ዘንድ ነው፡፡» (1ሳሙ. 17÷45-47) በማለት ትምክህቱ አምላኩ እንደሆነ አሳውቆአል፡፡ በዚህ ጊዜ ግን በሠራዊቱ ብዛት ሊመካና ሊታመን የጀመረ ይመስላል፡፡ ከዚህ በፊት የተረዳነውን እውነትና መገለጥ እንዳንረሳ መጠንቀቅ አለብን፡፡

ይህ የሕዝብ ቆጠራ ሐሳብ በሰይጣን አነሳሽነት ሲመጣለት የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆን አለመሆኑን እግዚአብሔርን አልጠየቀም፡፡ በልቡ የሠራዊቱን ብዛት የማወቅ ጤናማ ያልሆነ ምኞት ስለበረ ምኞቱን ብቻ ተከትሎ ይሄዳል፡፡ የእግዚአብሔር ሐሳብ ቢሆን ኖሮ በዘጸዓት ውስጥ ለሙሴ የሕዝብን ቆጠራ ሥርዓት እንደሰጠው ለዳዊት እስከነ አደራረጉ ይነግረው ነበር፡፡

«እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው፡-አንተ የእስራኤልን ልጆች ቁጥር ተቀብለህ በቆጠርሃቸው ጊዜ መቅሠፍት እንዳይሆንባቸው፣ በቆጠርሃቸው ጊዜ ከእነርሱ ሰው

ሁሉ እንደቁጥራቸው መጠን የነፍሱን ቤዛ ለእግዚአብሔር ይስጥ። አልፎ የሚቆጠር ሁሉ ግማሽ ሰቅል እንደ መቅደሱ ሰቅል ሚዛን ይሰጣል» ዘጸ. 30÷11-16።

የሕዝብ ቆጠራ ዝም ብሎ ተነሥቶ የሚደረግ እንዳልነበረ የሚያሳይ ክፍል ነው።

ዳዊት ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ ሕዝቡን ከቆጠረ በኋላ እግዚአብሔር በነቢዩ በጋድ በኩል ሦስት የቅጣት ምርጫ ይሰጠዋል። «ዳዊትም ጋድን እጅግ ተጨንቄአለሁ፤ ምሕረቱ ብዙ ነውና በእግዚአብሔር እጅ እንውደቅ፤ በሰው እጅ ግን አልውደቅ አለው» 2ሳሙ. 24÷14። ዳዊት የእግዚአብሔርን ምሕረት ከዚህ በፊትም የተለማመደ ስለነበረ በእግዚአብሔር ምሕረት ላይ ሲወድቅ እናያለን። «ዳዊትም ቸነፈሩን መረጠ» ቁ. 15። ከዳዊት ምርጫ በኋላ ቸነፈሩ በሕዝቡ መካከል ጀምሮ ከሕዝቡ ሰባ ሺህ ሰው እንደሞተ እናነባለን። ይህ ሕዝብ በዳዊት በደል ሞተ ማለት አንችልም እግዚአብሔር በአንዱ በደል ንጹሑን ሰው አያጠፋም። እግዚአብሔር ይህንን የዳዊትን በደል  ተጠቅሞ ቅጣት ያስፈልገው የነበረውንም ሕዝብ ጭምር ቀጣ ማለት እንችላለን። የሕዝቡ በደል ምን እንደነበረ ባይጠቀስም እግዚአብሔር በሥራው ሁሉ ጻድቅ እንደሆነና «ኃጢአት የምትሠራ ነፍስ እርስዋ ትሞታለች» ሕዝ. 18÷4። የሚል የእግዚአብሔር ቃል እንዳለ እናውቃለን።

ቸነፈሩ ሕዝቡን በመጨረስ ላይ እያለ ነቢዩ ጋድ ዳዊትን በኦርና አውድማ ለእግዚአብሔር መሠዊያ ሥራ ይለውና ዳዊት በአውድማው ላይ መሠዊያ ለመሥራት ወደ ኦርና ይሄዳል። ኦርናም ለዳዊት፡ - «ጌታዬ ንጉሡ እንደወደደው ወስዶ ያቅርብ፤ እነሆ ለሚቃጠል መሥዋዕት በሬዎች ለሚቃጠልም እንጨት የአውድማ ዕቃና የበሬ ቀንበር አለ።» በማለት ያለውን ንብረቱንና የዕለት ጉርስ የሚያገኝበትን የሥራ መሣሪያውን ለግብርና የሚጠቀምባቸውን በሬዎችና ቀንበሩን መሥዋዕት አድርጎ ያቀርባል። ዳዊት ግን «እንዲህ አይደለም ነገር ግን በዋጋ ከአንተ እገዛለሁ፣ ለአምላኬም ለእግዚአብሔር የሚቃጠል መሥዋዕት ያለ ዋጋ አላቀርብም አለው።» ሁለቱም ለእግዚአብሔር ርካሽና ዋጋ ቢስ የሆነ መሥዋዕት ማቅረብ እንደማይገባ የተረዱ ሰዎች ነበሩ። እግዚአብሔርም የእነዚህን ሰዎች ከልብ የሆነ መሥዋዕት አይቶ፤ «እግዚአብሔር ስለ አገሪቱ የተለመነውን ሰማ፣ መቅሠፍቱም ከእስራኤል ተከለከለ።» እውነተኛ ንስሐና ንጹሕ መሥዋዕት ባለበት ቦታ ሁሉ የእግዚአብሔር ይቅርታና የመቅሠፍት መከልከል አለ።

*Global Good News Literature*

*P.O.Box 451336*

*Los Angeles, CA 90045*

(C) Copyright 2013